አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝም እና ኮሙኒኬሽን

ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በቡድን ማስተማር ለተማሪ ውጤታማነት ያለው አስተዋጽኦ (በሙዱላ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት)

ለተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

መንበሩ አበጀ

ግንቦት 2005 ዓ/ም

የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በቡድን ማስተማር ለተማሪ ውጤታማነት ያለው አስተዋጽኦ (በሙዱላ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂደማኒቲስ፣የቋንቋ ጥናት፣የጆርናሊዝም እና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

ለተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

መንበሩ አበጀ

ግንቦት 2005 ዓ/ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂደማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝም እና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በቡድን ማስተማር ለተማሪ ውጤታማነት ያለው አስተዋጽኦ (በሙዱላ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት)

ለተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

መንበሩ አበጀ

ግንቦት 2005 ዓ/ም

የፈተና ቦርድ አባላት

_____	_____
አማካሪ	ፊርማ
አንዳርጋቸው አንተነህ (ዶ/ር)	_____
ፈታኝ	ፊርማ
ማርማ ገብሬ	_____
ፈታኝ	ፊርማ

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና

አጎጽሮተ ጽሁፍ

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ.....1

1.1 የጥናቱ ዳራ.....1
1.2 የጥናቱ ዓላማ.....4
1.3 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት.....4
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ.....5
1.5 የጥናቱ ወሰን.....5
1.6 የቁልፍ ቃላት እና ሐረጋት ፈቺ.....5

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት

2.1 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት.....8
2.1.1 የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ምንነት.....8
2.1.2 የተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ መርሆች.....11
2.1.3 የተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ጠቀሜታ.....12
2.1.4 በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የመምህሩ ሚና.....14
2.1.5 በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የተማሪዎች ሚና.....16
2.1.6 በተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ የቡድን ማስተማር ዘዴ.....18
2.1.6.1 የቡድን ማስተማር ዘዴ ምንነት.....19
2.1.6.2 የቡድን ማስተማር ዘዴ ጠቀሜታ.....19
2.1.6.3 የቡድን ማደራጃ መንገዶች.....21
2.1.6.4 በቡድን ማስተማር ዘዴ የመምህ ተግባር.....23
2.1.6.5 የቡድን ማስተማር ዘዴ ጠንካራ ጎኖች 25
2.1.6.6 የቡድን ማስተማር ዘዴ ደካማ ጎኖች.....26
2.1.7 የመማሪያ ክፍሎች አደረጃጀትና የተማሪዎች አቀማመጥ 27
2.1.8 በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የምዘና ስልት.....27
2.1.9 ተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ሁኔታዎች..29
2.1.10 የጽሕፈት ክሂል.....30
2.1.10.1 የጽሕፈት ክሂል ምንነት.....30
2.1.10.2 የጽሕፈት ትምህርት ዓላማ.....31
2.1.10.3 የጽሕፈትን ትምህርት አስቸጋሪ የሚያደርጉ ሁኔታዎች.....33
2.1.10.4 የጽሕፈት ክሂልን የማቀድና የማስተመማር መርሆች.....35

2.1.10.5 የጽሕፈት ክሂል አቀራረብ ዘዴዎች.....36
2.1.10.5.1 ውጤት-ተኮር አቀራረብ 36
2.1.10.5.2 ሂደታዊ አቀራረብ 41
2.1.10.5.3 ውጤት-ወሂደት አቀራረብ 45
2.2 የቀደምት ጥናታዊ ጽሑፎች ቅኝት.....46

ምዕራፍ ሦስት

የጥናቱ ዘዴ.....50
3.1 የናሙና አመራረጥ.....50
2.1.7 የቦታና የትምህርት ቤት ናሙና.....50
2.1.8 የክፍል ናሙና.....50
2.1.9 የምድብ ናሙና.....51
2.1.10 የሙከራዊ ቡድኑ የክፍል ውስጥ ክንውን ናሙና.....51
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች.....51
3.2.1 የቅድመ ችሎታና የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች.....51
3.2.2 የጽሑፍ መጠይቅ.....52
3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ.....53

ምዕራፍ አራት

የማስተማር ሂደትና የመረጃ ውጤት ትንተና.....54

4.1 የማስተማር ሂደት.....54
4.2 የመረጃ ውጤት ትንትና.....70
4.2.1 የቅድመ ችሎታ ምዘና ውጤቶች ትንተና.....70
4.2.2 የድኅረ-ችሎታ ምዘና ውጤቶች ትንተና.....74
4.2.3 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና.....78

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሓሳብ.....84

5.1 ማጠቃለያ.....84
5.2 የመፍትሔ ሓሳብ.....87

ዋቢ ጽሑፎች

አባሪ-አንድ የቅድመ- እና ድኅረ-ችሎታ መለኪያ ፈተና.....96

አባሪ-ስምንት ለማስተማሪያነት የተመረጠ የፍቅር እስከ መቃብር ቅንጫቢ.....109

አባሪ-ዘጠኝ የመሸጋገሪያ ቃላት ወይም ሐረጋት.....111

አባሪ-አሥር ሥርዓተ-ነጥብ.....112

አባሪ-አሥራ አንድ አንቀጽ.....114
አባሪ-አሥራ ሁለት የሥራ ደብዳቤ አጻፃፍ.....116
አባሪ-አሥራ ሦስት የሥራ ደብዳቤ ሞዴል 117
አባሪ-አሥራ አራት አስተዋጽኦ መንደፍ 119
አባሪ-አሥራ አምስት አስተዋጽኦ አነዳደፍ ማሳያ ሞዴል.....120
አባሪ-አሥራ ስድስት የድርሰት አፃፃፍ.....121
አባሪ-አሥራ ሰባት ለመከራ ቡድኑ የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ.....123
አባሪ-አሥራ ስምንት ድርሰት ለማረም የሚያስችል የነጥብ አሰጣጥ.....128

የሠንጠረዥ ማውጫ

ርዕስ ገጽ

አባሪ-ሁለት የመካከለኛ ቡድን የቅድመ ችሎታ ምዘና ውጤት መግለጫ.....98

አባሪ ሦስት የጥበቅ ቡድን የቅድመ ችሎታ ምዘና ውጤት መግለጫ.....100

አባሪ-አራት የመካከለኛ ቡድን የችሎታ ምዘና ውጤት መግለጫ 102

አባሪ-አምስት የጥበቅ ቡድን የችሎታ ምዘና ውጤት መግለጫ 104

አባሪ-ስድስት የመካከለኛ ቡድኑ የትምህርት ዕቅድ.....107

አባሪ-ሰባት የጥበቅ ቡድኑ የትምህርት ዕቅድ.....108

ምስጋና

አማካሪዬ ተባባሪ ፕሮፌሶር አረጋ ኃይለሚካኤል የጽሑፍም ይሁን የጽንሰ ሐሳብ ስህተቶችን በወቅቱ በማረም፣ግልጽ የሆነ ውይይት እንዳደርግ በአባታዊ አቀራረባቸው በማበረታታትና ገንቢ ሐሳብ በመስጠት ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ላደረጉልኝ ምሁራዊ ምክር ላቅ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

ለጥናቱ ትምህርት ቤቱን በመፍቀድ እና አሰፈላጊውን እገዛ በማድረግ ለተባበሩኝ የሙዱላ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የሥራ ኃላፊዎች፡-እንዲሁም የተማሪዎችን ፈተና በማረም፣ያላቸውን ልምድ በማካፈልና የተለያዩ ለጥናቱ አስፈላጊ ሥረዎችን በመሥራት እገዛ ላደረጉልኝ ጓደኞቼና የሥራ ባልደረቦቼ ለአቶ ዓለማየሁ ወጫቶ፣ ታይሥር ዓሊ፣ለአቶ መሐመድ ኑር፣ለአቶ ሲሳይ በቀለ፣ለአቶ ኑራሞ በላቸው እና ለአቶ ዝናቡ ኃይሌ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

በሓሳብና በፀሎት ማበራታቻዋ ላልተለየኝ ውዷ እናቴ ወ/ሮ ዳመነች ጃባሞ ዕድሜና ጤና ሰጥቶ እንዲያቆይልኝ እየተመኘሁ ከልቤ የመነጨ ምስጋና አቀርባለሁ።

በትምህርቱም ይሁን በጥናቱ ሥራ እገዛቸው ላልተለየኝ ወንድሞቼ አቶ ተገኔ አበጀ፣ያለቃ ከለላ አበጀ፣አቶ መጠጊያ አበጀ፣ ያለቃ መልካሙ አበጀ፣በፈቃዱ አበጀ እና ለአንዷ እህቴ ትዝታ አበጀ፣ እንዲሁም እንደ አባት በመሆን ዘወትር እገዛቸው ላልተለየኝ ለአቶ ሚካኤል ሳከሎ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በሥራው ላይ ጫና የሚያሳድሩ እና የሚፈታተኑ ሁኔታዎችን በመቋቋም ጥናቱም ይሁን ትምህርቱ በሚፈለገው መልኩ እንዲጠናቀቅ ከፍተኛ የሆነ መስዋእትነት በመክፍል ቀና የሆነ ትብብራቸውን ላደረጉልኝ ለአቶ አዳነ መካንጎ እና ለወ/ሮ ዓመለ ወርቅ ልዑል ሰገድ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

በመጨረሻም ከጎኔ በመሆን አሰፈላጊውን ሁሉ እገዛ ያደረገችልኝን ወ/ሮ ዓለም አዳነን ከልቤ አመሰግናለሁ።

አጎጽሮተ ጽሁፍ

ይህ ጥናት በሙዱላ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በሁለት ፈረቃ ከተመደቡት የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች በናሙናነት በተመረጡ 126 ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ነው። እነኝህ ለጥናቱ የተመረጡ ሁለት ቡድኖች ተጠኝ (Expermental) እና ጥብቅ (Controlled) በመባል የተከፈሉ ናቸው። በተጠኚነት (Expermental group) የተመረጡት ምድብ ተማሪዎች በአጥኚው አማካይነት እንዲማሩ የተደረገ ሲሆን በጥብቅ ሁኔታ (Controlled group) የተጠኑት ምድብ ተማሪዎች ደግሞ በመደበኛ መምህር እንዲማሩ ተደርጓል። የዚህ ጥናት ዓላማም የጽህፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዘዴ በቡድን ማስተማር ለተማሪዎች ውጤታማነት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በመከራ ማረጋገጥ ነው። ይህ ጥናት መጠናዊ (Quantitative) የምርምር ዘዴን በዋናነት የተከተለ ሲሆን ዓይነታዊ (Qualitative) የምርምር ዘዴንም በተጨማሪነት ተጠቅሟል። በመሆኑም የጥናቱን ውጤት አኃዛዊ መጠን ለመግለጽ ያመች ዘንድ ሁለቱም ቡድን የቅድመ ትምህርትና የድኅረ ትምህርት ዲዛይን (Two group pre-test) እና (post-test design) በሥራ ላይ ውሏል። አስተማማኝነቱን የበለጠ ለማጠናከር ሲባልም ጥናቱ በጽሑፍ መጠይቅ እንዲታገዝ ተደርጓል። ሁለቱም ምድቦች የቅድመ ትምህርት ምዘና ከተሰጣቸው በኋላ የመከራ ትምህርቱ ልምምድ ለስድስት ሳምንታት ያህል ተከናውኗል።በዚህ ክንውን ወቅትም ሁለቱ ምድቦች ተመሳሳይ ይዘትን በተለያዩ ዘዴዎች ከተማሩ በኋላ በተመሳሳይ ሰዓት እና ሁኔታ የድኅረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸዋል። ተጠኝ (Expermental) ምድቦች መማር ማስተማሩን አስመልክቶ የሚሰማቸውን አስተያየት በጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል። በዚህም መሰረት ከፈተናዎቹ የተገኙት ውጤቶች እንደሚያመለክቱት ሁለቱ ምድቦች በተፈተኑት በቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት የጎላ ልዩነት አልታየባቸውም። ይሁን እንጂ በድኅረ ትምህርት ፈተናቸው

የጎላ ልዩነት ታይቷል። ምክንያቱም የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዘዴ በቡድን የተማሩት ተማሪዎች በመምህር -ተኮር አቀራረብ ዘዴ ከተማሩት የበለጠ ውጤት ማስመዝገብ ችለዋል። ተጠኝ (Expermental) ምድቦች ከሞሉት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ደግሞ ተማሪዎች ከመምህር-ተኮር ዘዴ ይልቅ በተማሪ-ተኮር ዘዴ በቡድን ቢማሩ የጽሕፈት ክሂል ችሎታቸውን በከፍተኛ ሁኔታ ለመሳደግ እንደሚያግዛቸው አብራርተዋል።

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ

የሰው ልጅ ለሚያከናውነው ማንኛውም ተግባር ቋንቋ ቁልፍ መሳሪያ ነው። ለዕለት ተዕለት ተግባር፣ መልእክት በመቀበልና በማስተላለፍ ሂደት ቋንቋ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው።ማንኛውም ተማሪ የቋንቋ ብቃት ከሌለውና መልእክትን መረዳት ካልቻለ ምንም ትርጉም ያለው ተግባቦት ሊያከናውን አይችልም።

የትምህርት ዋና ዓላማ የተማሪዎችን ዕውቀት፣ ክሂሎትና አመለካከት ማሳደግ ነው።ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ በመማር-ማስተማሩ ሂደት፣ዘዴውና የትምህርት ውጤታማነት የተቆራኙ በመሆናቸው የተለያዩ ስነ ዘዴዎችን መተግበር ተገቢ ነው።

የማስተማሪያ ዘዴዎችና ክንውኖች ተፈጥረው በአገልግሎት ላይ የሚውሉት በመማር ማስተማሩ ሥራ ውጤታማነት ላይ ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ስለሆነ ነው።

የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በየጊዜው የሚለዋወጥ፣የሚያድግና እየዳበረ የሚመጣ ሂደት ነው።በዚህ ሂደት ውስጥ ለብዙ ዘመናት ያገለገለው በመምህር ብቻ የሚመራው ባህላዊ በጠመኔ የመጻፍና የመናገር ዘዴ "Traditional chalk and talk teaching method" እና ተማሪዎች በነጻነት እኩል የሚጋሩበትና የሚሳተፉበት ተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ከፍተኛ እውቅና አላቸው። ተማሪ-ተኮርና መምህር-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎችን ምሁራን በተለያየ መንገድ ገልጸዋቸዋል።

እንደ Rogers (2002፣22) እና Plass (1998፣44) አገላለጽ፣የአቀራረብ ዘዴዎቹ የተለያዩ ስያሜዎች ቢኖራቸውም ይበልጥ እውቅና አላቸው ብለው የጠቀሷቸው፤

- መምህር-ተኮር እና ተማሪ-ተኮር (Teacher-Centered Vs Student-centered)
- ተቀባይነት ያለው (ተመራጭ) እና ተመራጭ ያልሆነ አቀራረብ (Conventional Vs Non-Conventional)
- ቀጥተኛ አቀራረብና ቀጥተኛ ያልሆነ አቀራረብ (Direct Instruction Vs Indirect Instruction)
- ባህላዊ አቀራረብና ባህላዊ ያልሆነ /ዘመናዊ/ አቀራረብ (Traditional Vs Non- Tradtional /Modern/ Instruction) ናቸው።

Rogers (2002፣12) Borich (1992)ን ጠቅሰው እንደገለጹት፣ሙያዊ ቃላቱን ቀጥተኛ የማስተማር ዘዴ በሚል ስር መምህር-ተኮር፤ባህላዊ፣ገለጻዊ፣ፈላጭ ቆራጭ፣ ተመራጭ ያልሆነ፣ ጨቋኝ፣ ወዘተ. በማለት ማካተት ይቻላል።ቀጥተኛ ያልሆነ አቀራረብ ዘዴ ደግሞ ተማሪ-ተኮር፣ዲሞክራሲያዊ፣ንቁ፣ራስ-መር፣ተለዋዋጭ፣ ተመራጭ በማለት አብራርተዋል ።

በተጨማሪም እነዚህን ዘዴዎች በተመለከተ እነ Moore (2001)፣ McCombs (1997)፣ Lue (2000) እና Tudor (1996) የማስተማሪያ ዘዴዎች መምህር-ተኮርና ተማሪ-ተኮር አቀራረቦች በመባል በሁለት እንደሚከፈሉ ገልጸዋል።

ምሁራኑ እንደሚሉት፣መምህር-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተለምዷዊና እድሜ-ጠገብ የማስተማሪያ ስልት ነው።በትምህርት ሂደቱም በአብዛኛው የመምህሩ የበላይነት ጎልቶ ይንጸባረቅበታል።ከዚህም የተነሳ ተማሪዎች በትምህርቱ ንቁ ተሳታፊ አይሆኑም። በአንጻሩ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች በትምህርት

ሂደቱ ግንባር ቀደም ተሳታፊዎች ናቸው። ይህ አቀራረብ ተማሪዎች በአብዛኛው በራሳቸው ጥረት እንዲማሩ ዕድል ይሰጣል። አቀራረቡ ተማሪዎችን በብቃት የሚያሳትፍ የማስተማሪያ ዘዴ ነው።

በመሆኑም ተማሪው በትምህርቱ ሂደት መሪ ተዋናይ የሚሆንበትን ዕድል ይሰጣል። መምህር-ተኮር አቀራረብ ግን በአብዛኛው የመምህሩ የበላይነት ጎልቶ የሚታይበት ነው። ተማሪውን ንቁና አቻዊ ተሳታፊ ሳይሆን ተመልካች ያደርገዋል።ስለሆነም ተማሪ-ተኮር አቀራረብ በተለይ ለቋንቋ ትምህርት ተመራጭ ነው። ምክንያቱም ተማሪው ያለው ውስጣዊ የቋንቋ ችሎታ በትምህርቱ ሂደት ተሳታፊ በመሆን እያዳመጠ፣እየተናገረ፣እያነበበና እየጻፈ የሚያሳድግበትን ዕድል ስለሚሰጥ ነው።በዚህም መሰረት በኢትዮጵያ ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ አዲስ የትምህርት ፖሊሲ ተቀርጾ በስራ ላይ ውሏል (ትምህርት ሚ/ር፣1994)።

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ተማሪን አሳታፊ የሆነ፣የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን ለማቀናጀት የሚያስችል የማስተማሪያ ዘዴ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪ- ተኮር የትምህርት አቀራረብ ተግባራዊ በመሆን ላይ ነው። ተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ Ur (1996:17) እንደሚገልጹት፣ተማሪውን አሳታፊ፣ የመረዳት፣ የመተርጎም፣ የማብራራትና ሃሳብ የማመንጨት ችሎታና ክሂሎቱንም የሚያዳብር በመሆኑ በመስኩ ባለሙያዎች ዘንድ ትኩረት አግኝቷል። እንዲሁም ከአንድ አቅጣጫ ከመምህሩ ወደ ተማሪው ብቻ ይደረግ የነበረውን መስተጋብር ከተማሪው ወደ ተማሪው፣ ከተማሪው ወደ መምህሩ የሃሳብ ልውውጥ እንዲኖር አድርጓል ።

ሆኖም ይህ ተማሪ-ተኮር ዘዴ በፖሊሲ ደረጃ በትምህርት ሥራ ላይ ቢውልም የአተገባበር ችግሮች እንዳሉት ሙሉጌታ (1996) እና Fisseha (2001) በጥናቶቻቸው ጠቁመዋል።

1.2 የጥናቱ ዓላማ

የቋንቋ ትምህርትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለተማሪዎች ለማድረስ የማስተማሪያ ዘዴ ዓይነተኛ ሚና አለው። የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል፣ በከምባታ ጠምባሮ ዞን፣ ጠምባሮ ወረዳ፣ በመዱላ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በቡድን ማስተማር ለተማሪ ውጤታማነት ያለው አስተዋጽኦ ምን እንደሚመስል ሙከራዊ ጥናት በማካሄድ ማጣራት ነው። በሥሩም የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች አሉት።

- በመምህር-ተኮር እና በተማሪ-ተኮር አቀራረቦች መካከል የታየው የተማሪ ውጤት ምን ይመስላል?
- በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሚገጥሙ ችግሮች ምን ምንድን ናቸው?
- ለገጠሙት ችግሮችስ መፍትሄ የሚሆኑት ሓሳቦች የትኞቹ ናቸው? የሚሉ ናቸው።

1.3 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚውን በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ለማካሄድ ያነሳሳው ምክንያት አብዛኞቹ ተማሪዎች ለጸሕፈት ክሂል የሚሰጡት ቦታ ከተቀሩት የቋንቋ ክሂሎች ጋር ሲነፃፀር እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ በብዙ ምሁራን ይገለጻል፤ስለሆነም ይህንን የጽሕፈት ክሂል በአሁኑ ወቅት ተቀባይነትን እያገኘ በመጣው በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በቡድን ማስተማር ምን ያህል ውጤታማ እንደሚያደርግ ለማረጋገጥ ያለው ፍላጎት ነው።

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች ውጤታማነት ላይ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው። በዚህ ጥናት የተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በተማሪዎች ውጤታማነት ላይ ያለውን ሚና በሙከራዊ ጥናት (Expermental Research) በመፈተሽ ያለውን ተጨባጭ መረጃ ማሳየት ነው።በአጠቃላይ ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፤

1. ተማሪ ተኮር ዘዴ ለተማሪ ውጤታማነት ያለውን ፋይዳ ያሳያል፤
2. ጥናቱ ለመምህራንና ለትምህርት ባለሙያዎች ተማሪ-ተኮር ዘዴን እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ግብአት ይሰጣል።
3. ወደፊት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥ ጥናቶችን ለሚያካሂዱ አጥኚዎች በመነሻነት ያገለግላል።

1.5 የጥናቱ ወሰን

- የጥናቱ ቦታ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ በከምባታ ጠምባሮ ዞን፣ ጠምባሮ ወረዳ፣ ሙዱላ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት ነው።
- ጥናቱ በ2005 ዓ/ም ዘጠነኛ ክፍል በሚማሩት ተማሪዎች ላይ ተካሂዷል።
- በመማር-ማስተማር ሂደት በርካታ ጉዳዮች ያሉ ቢሆንም ይህ ጥናት ግን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በቡድን ማስተማር ዘዴ ሙከራዊ ጥናት ያተኩራል።
- ጥናቱ በጽሑፍ ክሂል ላይ ያተኩራል።

1.6 የቁልፍ ቃላት እና ሐረጋት ፈቺ

ከመገኛ ቋንቋቸው ተተርጉመው የአማርኛ ቋንቋ ፍቺ የተሰጣቸው ቃላት በጥናቱ ውስጥ የሚያስተላልፉት ሓሳብ ለአንባቢ ግልጽ እንዲሆን ብያኔያቸው በፊደል ተራ ቅደም ተከተል ቀርቧል።

- መላምት (Hypothesis)

አንድ ምርምር ከተካሄደ በኋላ ሊረጋገጥ የሚችል "ሊሆን ይችላል" ተብሎ የሚታሰብ ውጤት ነው።

- ስነ ዘዴ (Methodology)

ስነ ዘዴ ንድፈ ሓሳባዊ ሳይሆን ተግባራዊ የሆነ፣የጽሕፈት መማሪያ ግብአቶች የሚቀርቡበት፣ንድፈ ሓሳብ ወደ ተግባር የሚለወጥበት፣ይዘትና ክሂል የሚመረጥበትና በቅደም ተከተል የሚተገበርበት ከአቀራረብ የሚፈልቅ ሆኖ ጥቅም ላይ ይውላል።

- ቲ-ቴስት

ቲ-ቴስት አንድን ቡድን ወይም ናሙና ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ ተለዋዋጮች አንፃር ያለውን የባህሪ ለውጥ ለማጥናት ወይም ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ቡድኖችን ወይም ናሙናዎችን ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ተለዋዋጮች አንፃር ያላቸውን የባህሪ ተመሳሳይነት ለማወዳደር ከሚያገለግሉ ከተለያዩ ፓራሜትራዊ መፈተሻ ዓይነቶች አንዱ ነው (ያለው 2001፣274)።

አቀራረብ (Approach)

አቀራረብ በቋንቋ ማስተማር ተግባር እና የመርህ መገኛ እንዲሁም ስለ ቋንቋ ባህርይና ስለ ቋንቋ መማር የሚገልጽ ንድፈ ሓሳብ ነው። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የጽሕፈት አቀራረብ አጠቃላይ ንድፈ ሓሳባዊ መርሆችን የያዘ፣ ልዩ ልዩ የትግበራ ዘዴዎችን ያከተተ፣ውስን የማስተማር ቴክኒኮችን እና ክንውኖችን የሚገልጽ ቃል ነው።

- **የሠንጠረዥ ዋጋ**

የሠንጠረዥ ዋጋ የሚባለው የስሕተት ይሁንታ መጠኑን፣የፍተሻውን ዓይነትና የነፃነት ደረጃውን መሰረት አድርጎ በሠንጠረዦች ላይ የሚገኝ ዋጋ ነው። ለተለያዩ የስታቲስቲካዊ ዘዴዎች የተለያዩ የሠንጠረዥ ዋጋዎች ያሉ ሲሆን አገልግሎታቸውም ከሚገኙት ዋጋዎች ጋር በማወዳደር የተመቱትን መላምቶች በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ወይም መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ነው (ያለው 2001፣273)።

- **የነፃነት ደረጃ**

የነፃነት ደረጃ ሂሳባዊ እሳቤ ሲሆን መሰረት የሚያደርገው የጥናት ተሳታፊዎችን ብዛት ነው። ከተሰጡን ውጤቶች (የጥናት ተሳታፊዎች ብዛት) መካከል ለማቀያየር የሚኖረንን ነፃነት የሚያሳይ ነው (ያለው 2001፣273)።

- **የጉልህነት ደረጃ (የስሕተት ይሁንታ መጠን)**

የጉልህነት ደረጃ ወይም የስሕተት ይሁንታ መጠን ሲባል ከመቶ እጅ በምን ያህል መጠን አልቦ መላምቱን በስሕተት ውድቅ ልናደርገው እንደምንችል የሚያመላክት ነው(ያለው 2001፣272)።

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳናት

2.1 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

2.1.1 የተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ምንነት

የተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ የተጀመረው በ16ኛ ክፍለ ዘመን በችኮዝላቪያ ምሁራን እንደሆነ Amanu (2005:22) ገልጸዋል። ይሁን እንጂ ይህ አቀራረብ በስፋት እየታወቀና ተቀባይነትን እያገኘ የመጣው በ1950ዎቹ ገደማ እንደሆነ Wassihune (2006) ያስረዳሉ።

በተጨማሪም Sirak (2000) እና Terefe (2005) ይህ አቀራረብ ተቀባይነትን እንዲያገኝ ያስቻሉት ምክንያቶች፤ የተለያየ የመማር ስልት ያላቸውን ተማሪዎች ማዕከል ማድረጉ፣ ከሕብረተሰቡ ጋር ተግባብቶ ለመኖር ልምዶችን መቅሰም ማስቻሉና በተማሪዎች፣ ዕውቀት፣ክላኅትና ስሜት ላይ የተመሰረተ ትምህርት ለማቅረብ ማስቻሉ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ የክፍል ውስጥ ተስተምህሮ ሂደትን ማራኪ በማድረግ፣ የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀትና የሕይወት ልምድ መሰረት በማድረግና መሰረታዊ የመማር ፍላጎትንና የተረድኦት አቅምን ያጎለብታል። ስለሆነም ተማሪዎች የሚያገኙትን አዲስ ትምህርት ከቀደመ ዕውቀታቸው ተነስተው ለመረዳትና ለማደራጀት እንዲሁም ማሕበራዊ ሕይወትን ለማጠናከር የሚያግዝ ነው (Tsegaye 2001:5)።

በድሩ (1990:9) ደግሞ በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ተማሪው ትምህርቱን በራሱ የመማር ፍላጎት፣ስሜት፣ተነሳሶትና ጥረት አማካይነት ያከናውናል።

ስለሆነም ተማሪው ከመምህሩ ጥገኝነት ተላቆ ትምህርታዊ ተሳትፎውን በማሳደግ እውነተኛና ዘላቂ የሆነ የባህርይ ለውጥ እንዲያመጣ ያስችላል በማለት ገልጸዋል።

የተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ዘዴ በንቃት መማር፣መስተጋብራዊ መማር፣በመስራት ወይም በማድረግ መማር፣በመሳተፍ መማር፣እመርታዊ መማር በመባል እየተቀያየረ እንደሚያገለግል Brands and Gunnis (1991:24) የተለያዩ ምሁራንን በመጥቀስ አብራርተዋል። የተዘረዘሩት የምሁራን ሐሳቦች የተለያዩ ቢሆኑም ሁሉንም የሚያስተሳስራቸው የጋራ ባህርይ ተማሪዎች የሚያደርጉት ንቁ ተሳትፎ ነው።

ተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ሁሉንም ሙያዊ ስያሜዎች አጠቃሎ በመያዙ ተመራጭ ስለመሆኑ Brands and Gunnis (1991:24) ይገልጻሉ።

McCombus and Whistler (1997:1) የትምህርት አቀራረብ ዘዴው ተማሪዎች የግልና የቡድን ብቃታቸውን የሚያሳድጉበት፣የትምህርት ተፈጥሯዊ ችሎታቸውን፣ ልምዳቸውን፣ ትኩረታቸውን፣ ዳራዊ ዕውቀታቸውን፣ ፍላጎትና ተሰጧቸውን፣ ምኞትና ብቃታቸውን እንዲያንጸባርቁ የሚያስችል ዘዴ ነው።

እንደ Dirribsa (2005:7) አገላለጽ ተማሪዎች ሁል ጊዜ በትምህርት የሚጠመዱ በመሆናቸው አዳዲስ ሐሳቦችን ያፈልቃሉ፤ የሚቀርቡ ጥያቄዎችንና መልሶችን በጸጋ ከመቀበል ይልቅ ይጠይቃሉ፤ ይከራከራሉ፣ ይወያያሉ፣ ያብራራሉ፣ አሳማኝ የሚሏቸውን ነጥቦች ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ ያንጸባርቃሉ፤ አዳዲስ ሃሳቦችን ያፈልቃሉ፤ ከሕይወት ልምዳቸው ጋር በመነሳት ለችግሮች መፍትሔ ይፈልጋሉ።

የሺጥላና ሌሎች (1996:1) ስለ ተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ሲገልጹ የሚሰጠው ትምህርት ተማሪዎችን በባለቤትነት እንዲሳተፉ ስለሚጋብዛቸው ብዙ እንዲያነቡ፣ በጥልቀት እንዲወያዩ፣ ብዙ እንዲያውቁ፣ ሐሳብ መቀበልንና መስጠትን

እንዲያካብቱ፣ ከአከባቢ ጋር እንዲመሳሰሉና በድርጊት እንዲሳተፉ ያስችላቸዋል በማለት ያብራራሉ።

Amare et al. (1998)፣McCombus and Whistler (1997) እና Tudor (1996) ተማራ- ተኮር የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች የሚማሩበት፣መምህሩ ለመማር ማስተማሩ ሥራ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥርበት ዘዴ ነው ይላሉ።በዚህ የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ትልቁን ሚና የሚጫወቱት ተማሪዎች የእርስ በእርስ መስተጋብር ውስጥ ተሳታፊ በመሆን በክፍል ውስጥ ነባራዊ ሁኔታን ይፈጥራሉ።

በዚህ ዘዴ የሚማሩ ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ ዕውቀትን ይገበያሉ፣ የገበዩትንም ዕውቀት ከቀደመ ዕውቀታቸው ጋር በማዛመድ አዲስ የአጠቃቀም ልምድንና ብልሃትን ያዳብራሉ። በቀሰሙትም ዕውቀት ተጠቅመው ማሕበራዊና ባሕላዊ ኃላፊነቶችን በመለማመድና በመሳተፍ ውጤታማ በሆነ መንገድ ችግር ፈችና መፍትሔ-ሰጭ አካል እንዲሆኑ የትምህርት አቀራረብ ዘዴው ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።የትምህርት አሰጣጡ በችግር ፈችነት ላይ ያተኮረ ሆኖ እንደ ቀድሞው በቃል ነባቢነት ወይም ጥቁር ሰሌዳና ጠመኔ ብቻ በመጠቀም መምህር-ተኮር በሆነ የማስተማር ዘዴ መምህራን እንዲጠቀሙ የሚያደርግ በተቃራኒው ተማሪዎች ልዩ ልዩ መልመጃዎች እየሰሩ፣ እየጠየቁ፣ እየተመራመሩ ትምህርቱን የሚቀስሙበትን ዘዴ በስራ ላይ የሚያውል ነው (ትምህርት ሚኒስቴር 1994:27)።

O'Neill and McMahon (2005:12) ተማራ-ተኮር አቀራረብ የሚታይበት ባህርይ በማለት እንደገለጹት አቀራረቡ ለተማሪዎች አእምሮ፣ስሜትና አካል ዕድገት ትኩረት በመስጠት በራስ የመተማመን ስሜትን ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደረሰ፣ ተሳትፎን፣ የቀደመ ዕውቀትንና ልምድ መጠቀምን፣ አዳዲስ ኃላፊነት መለማመድን፣ ለተለያዩ አመለካከቶች ዋጋ መስጠትን እና በጥሩ ምግባር ሓሳብ ማራመድን እንዲያጎለብቱ ያደርጋል በማለት ይገልጻሉ።

ተማራ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችንና የግምገማ ስልቶችን ለመጠቀም የሚያስችል በመሆኑ ትምህርታዊ መተጋገዝንና አቻዊ ግምገማን ያደፋፍራል። በመሆኑም ተማሪዎች ለትምህርቱ የባለቤትነትና የኃላፊነት ስሜትን እንዲያጎለብቱ ይረዳል። ይህም በመምህሩና በተማሪው መካከል ጥሩ የሆነ የእርስ በርስ መከባበር እንዲፈጠር ለማድረግ አመቺ እንደሆነ Lue (2000:12) ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ ተማራ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች አንዱ ሌላውን በመጣል ልቆ ለመታየት የሚያሳዩትን መሸቀዳደም በማስቀረት በምትኩ እርስ በርሳቸው የመረዳዳት፣ የመተጋገዝና አብሮ የማደግ አመለካከት እንዲያጎለብቱ እገዛ ያደርጋል።

2.1.2 የተማራ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ መርሆች

የተለያዩ ምሁራን የተማራ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች ከየክፍለ ትምህርቱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲፈጥሩ በማድረግ በተማሪዎች መካከል የሚከናወነው ተግባቦታዊ መስተጋብር ይበልጥ እንዲጠናከር የማደፋፈር፣ የተማሪዎችን ችሎታና የመማር ስልት ልዩነት ከግምት ውስጥ የማስገባት፣ መምህሩ ማስተማር ከፈለገው ነገር ይልቅ ተማሪ መማር ለሚፈልገው ቅድሚያ የመስጠትና በትምህርቱ መጨረሻ ስሜትን የሚያነቃቃ ምግበ መረጃ የማቅረብ መርሆች እንዳሉት ገልጸዋል። ከነዚህም መካከል Michael, etal.(2000)፣ Temechegn (2002) እና ሙሉጌታ (2002) ተማራ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ መርሆችን እንደሚከተለው አብራርተዋል፤

- የተማሪዎችን የተለያየ ችሎታና የመማር ስልት ያገናዘበ ትምህርት ማቅረብ፤

- ተማሪዎች የቀረበውን የትምህርት ይዘት መሰረት በማድረግ ርዕሶችንና ጽንሰ ሐሳቦችን የመምረጥ ነጻነታቸውን ከፍ ማድረግ
- ተማሪዎች በቡድን በትብብር የመማርና በንቃት የመሳተፍ አቅማቸውን ማጎልበት
- በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህራን፣መማሪያ መጻሕፍት፣ተማሪዎች የትምህርቱ ምንጭ መሆን፤
- የተማሪዎችን የህይወት ልምድ ያገናዘበ ትምህርት ማቅረብ፤
- የተማሪዎችን እውነተኛ ፍላጎት በማነሳሳት ነባራዊነት፣ግልጽነት፣ተቀባይነት፣ አድናቆት፣ጥልቅ ምልከታና ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ማድረግ፤
- ተማሪዎች በግምገማ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ አቅም በመፍጠር እርሰ በርስ እንዲተራረሙ ማደፋፈር፤
- የሚቀርበው ትምህርት የተማሪዎችን የባህርይ ለውጥ የሚያመጣ መሆን፤
- በትምህርቱ ጊዜ መምህራን አመቻች መሆን፤
- አበራታች ምኃቤ ምላሽ መስጠት የሚሉት ናቸው።

2.1.3 የተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ጠቀሜታ

ተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ዘዴም ተማሪዎች በታላሚው የቋንቋ ትምህርት ግብ መች እንዲሆኑ፣ በቡድን ተባብረው እንዲሰሩ፣ ዕውቀትን እንዲያስሱ፣ ኃላፊነትን እንዲለማመዱ እና በእርግጠኝነት ለትምህርታቸው ያላቸውን ኃይል ሁሉ አሟጠው እንዲጠቀሙ የሚያደርግ ዘመናዊ ዘዴ ነው (Dejene et al,. 2007፡119)።

ይህ አቀራረብ ተማሪዎች ከመምህራን ጥገኝነት ተላቀው በራሳቸው መንገድ የተለያዩ ክንውኖች ማድረግን፣ መመራመርን፣ መፍጠርን፣ መጠየቅን፣ መወያየትን፣

ይህ አቀራረብ ተማሪዎች ከመምህራን ጥገኝነት ተላቀው በራሳቸው መንገድ የተለያዩ ክንውኖች ማድረግን፣ መመራመርን፣ መፍጠርን፣ መጠየቅን፣ መወያየትን፣ መከራከርን እንዲያጎለብቱ፣በመካከላቸውም የመተሳሰብና የመተባበር ባህል በማሳደር የተግባቦት ብቃታቸውን እንዲያዳብሩ እገዛ ያደርጋል።ይህም ትምህርቱ ከንድፈ ሓሳብ ይልቅ በተግባር ልምምድ ተደግፎ የሚቀርብ በመሆኑ ጠቀሜታው ከፍተኛ እንደሆነ እነ Lue (2000፡3) እና Tsegaye (2001) ይገልጻሉ።

ከዚህም በተጨማሪ ተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በተማሪዎችና በመምህራን መካከል የሚታዩ ክፍተቶችን በማጥበብ ተማሪዎች ለትምህርታቸው ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋል።

እንደ Bentley (1998፡32) አገላለጽ ዘዴው ተማሪዎች በቡድን በመሆን እርስ በርሳቸው የሚረዳዱና ነቅተው የሚሳተፉ በመሆናቸው ለትምህርቱ ቅርብ እንዲሆኑ እገዛ ያደርጋል።መምህራኖቻቸው የተጨናነቀ መረጃ በተካታተይ ከመስጠት ይልቅ ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ ግንዛቤያቸውን እንዲያጎለብቱ እገዛ ለማድረግ ምቹ ሁኔታዎች ይገጥሟቸዋል። ይህም የመማር-ማስተማር ሂደቱን ውጤታማ ያደርገዋል።

ምሁሩ አያይዘው እንዳብራሩት፣ የትምህርት አቀራረቡ ተማሪዎች የተለያዩ ክንውኖችን በመሞከር ጠቃሚና ጠቃሚ ያልሆኑ አመለካከቶችን መፈተሽና በቀላሉ መለየት እንዲችሉ የሚያበረታታ በመሆኑ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ የመስራት ልምድን እንዲያዳብሩ ኃላፊነትን በመውሰድ ስለ ራሳቸው፣ ስለ ቤተሰባቸውና ስለ ማሕበረሰባቸው ሰፊ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያግዛል። በመሆኑም ተማሪዎች ማሕበራዊ ችግሮችን ሊፈታ የሚችል መፍትሔ የመሰንዘር ኃላፊነትን እንዲያጎለብቱ የማስቻል ጠቀሜታ እንዳለው ገልጸዋል።

Plass (1998:313) በበኩላቸው የትምህርት አቀራረብ ዘዴው ተማሪዎች በሚማሩት ትምህርት ዙሪያ ክሂሎታዊ ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ የማገናዘብ፣ የመተንተንና ሂሳዊ አስተሳሰብ የማራመድ፣ አእምሯዊ ክሂሎታቸውን እንዲያጠናክሩ ሁል ጊዜ ራስ-መርና ነጻ በመሆን ኃላፊነትን እንዲወስዱ፣ ከግላዊ የውድድር ስሜት ወደ ቡድናዊ የውድድር ስሜት እንዲያድጉ፣ ጤናማ የሆነ አንድነት እንዲያዳብሩ፣በአቻ ቡድን ውስጥ ኃላፊነትን መቀበልና ተጠያቂነት ባለው መንገድ መከራዎችን በማከናወን አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ እገዛ ያደርጋል ብለዋል።

በአጠቃላይ ተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች ከማዳመጥ ይልቅ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ አስተሳሰብ እንዲያጎለብቱ፣ የራሳቸውን ፍላጎትና ዓላማ እንዲያንጸባርቁ፣ የታጨቀ መረጃ ከማስተላለፍ ይልቅ ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ፣ በነጻነት እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩ፣ እንዲጠይቁ፣ እንዲተነትኑ፣ ማስረጃ እያጣቀሱ እንዲያብራሩ የማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

2.1.4 በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ የመምህሩ ሚና

ጥሩ የትምህርት አቀራረብና አተገባበር የትምህርት ግብን ውጤታማ ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።ይህንን እውን ለማድረግ ውጤታማ የትምህርት አቀራረብ ዘዴ፣መምህራን፣ተማሪዎች፣የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣የትምህርት ስልት፣ወዘተ. ወሳኝ ሚና አላቸው።

እንደ Abraham et al. (1999:23) እና Plass (1998:318) አገላለጽ፣ በተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ መምህራን ወሳኝ ሚና አላቸው።ይህም የመምህር ስራ በትምህርት ክንውኑ ተማሪዎች ከፍተኛ ደረጃ በደረሰ የማሰብ ክሂልና ዕውቀት እንዲገልጹ ነጻነት መስጠት፣ትምህርቱ ማራኪና አስተማሪ እንዲሆንና ተማሪዎች የተግባቦት ብቃታቸውን በማዳበር ችግር ፈች መሆን እንዲችሉ ማመቻቸት፣

ተማሪዎች መረጃዎችን ማነጻጸር፣ መተንተን፣መገምገምና በተለያየ መንገድ ማስረዳት እንዲችሉ የማስተባበር፣ የማደራጀት የትምህርት ይዘቱንም ማራኪ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በዚህ አቀራረብ የመምህሩን ሚና በተመለከተ Rogers (2002፡19) ሲገልጹ የሚከተለውን ብለዋል፤

- የትምህርቱን ዓላማ ማስተዋወቅ
- ለትምህርቱ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን መጠቆም
- የተለያዩ ተግባራትን የአሰራር ስልት ማሳየት ወይም አቅጣጫ ማመላከት
- የተሰሩ ስራዎችን በመከታተል ማረምና ገንቢ ምጋቤ ምላሽ መስጠት
- የተማሪዎችን የተለያየ የመማር ስልት መለየት
- የተማሪዎችን የመማር ለውጥ ማጥናት
- ከተለያዩ ተማሪዎች የሚሰነዘሩ ጥያቄዎችን፣መልሶችንና አስተያየቶችን እኩል በሆነ መንገድ ማስተናገድ
- በመማር ማስተማሩ ሂደት አነቃቂና ማራኪ ድባብ እንዲፈጠር ማድረግ
- በክፍል ውስጥ የግልና የቡድን ስራ በመስጠት ተዘዋውሮ መመልከትና ችግር ሲኖር ማስተካከያ መስጠት
- በተቻለ መጠን በቡድን ውይይት ጊዜ እንደ አንድ የቡድን አባል በመሆን መሳተፍ የሚሉትና የመሳሰሉት ናቸው።

በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉና ውጤታማ እንዲሆኑ ከትምህርት ዕቅድ እስከ ምዘና ድረስ ባለው ሂደት መምህሩ ትልቅ ኃላፊነት አለበት። ይህ ኃለፊነት ግን በመምህር-ተኮር አቀራረብ ካለው ክንውን ጋር ተመሳሳይነት የለውም (Aggrawal 1996:66)::

እንዲሁም በዚህ አቀራረብ መምህር የመማር-ማስተማሩን ሂደት ማራኪ በማድረግ በተማሪዎች ዘንድ የመማር ተነሳሶትን የሚፈጥር፣ትምህርቱን ፍትሓዊ በሆነ መንገድ የሚያቀርብና የታቀደውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችል የጠለቀ ሙያዊ ዕውቀትና ተፈጥሯዊ ብስለት ያለው መሆን እንዳለበት (Tudor፣1996) ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ መምህራን በተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ዘዴ በሚያስተምሩበት ወቅት ተማሪዎችን ለትምህርቱ በማዘጋጀት ስለ ትምህርቱ ግብ እንዲያውቁና የቋንቋ፣ የስሜት፣ የአመለካከት፣ የዕውቀትና የክሂሎት ዕድገታቸውን እንዲያጎለብቱ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። ይህን የትምህርት ግብ ውጤታማ ለማድረግ የተማሪዎችን ፍላጎት መረዳት፣ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መምረጥና መጠቀም፣ ኃላፊነትን ማካፈልና ሁሉንም ተማሪዎች በእኩልነት ማየት የማይታለፍ ተግባር ነው (Rogers 2002፣ Plass 1998)።

2.1.5 በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የተማሪዎች ሚና

በዘመናዊ የትምህርት አቀራረብና አተገባበር ተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ለተማሪዎች ከፍተኛ ትኩረትና ኃለፊነት በመስጠት የጎላ ሚና እንዲኖራቸው አድርጓል።ይኸውም ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ክንውን ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ፣ ይወያያሉ፣ ይጠይቃሉ፣ የተለያየ ሐሳብ ያፈልቃሉ፣ የአቻዎቻቸውን ሐሳብ ማክበርን ይለማመዳሉ።በመሆኑም ለአዳዲስ ዕውቀቶች የሚኖራቸው ጉግት ከፍተኛ ይሆናል።

እንደ O'Neill and McMahon (2oo5) አገላለጽ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች መረጃን ከመምህራቸውና ከመማሪያ መጽሐፍ መቀበል ብቻ ሳይሆን በግል፣ በጥንድና በቡድን በጋራ በመሆን ይሰበስባሉ፤ በብልሃት ይመዘግባሉ፤ ይተነትናሉ፤ ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ፤ ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎቻቸውን ተጠቅመው የተግባቦት

ተጠቅመው የተግባቦት አቅማቸውን ያጎለብታሉ፤ ለጥያቄዎችና ችግሮች መፍትሄ ይፈልጋሉ፤ ኃላፊነትን በመለማመድ ትምህርቱን ከሕይወታቸው ጋር እያያያዙ ይተጋሉ።

እነ Nunan (1988)፣Tilaka (1998) እና Amanu (2005) የተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በተማሪዎች ዘንድ ዘላቂ የሆነ ለውጥ እንደሚያስገኝ በመጠቆም ያሉትን ተግባራት እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ፤

- በትምህርት ሰዓት ፍጠ ተመልካች ከመሆን ይልቅ በንቃት መሳተፍ
- በትምህርታዊ ጉደዮች ላይ ኃላፊነትን መቀበል የእኔነት ስሜት መፍጠር
- የራስን የመማር ልምድ መለየት
- በትምህርታዊ ጉዳዮች ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉ ምክንያታዊ መሆን
- የግልና የቡድን ሥራዎችን መሥራትና መምራት መቻል
- የተሠሩ ሥራዎችን በቃልም ሆነ በጽሑፍ በክፍል ውስጥ ማቅረብ
- ግልጽ ያልሆኑ ጽንሰ ሐሳቦችን መጠየቅና ለሚጠየቁ ጥያቄዎችም መልስ መስጠት
- ከመምህራን ጋር በመተባበር የትምህርት ይዘቶችንና የምዘና ስልቶችን መምረጥና መወሰን ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው።

Michael, et al. (2002) Kaemanee (2002)ን በመጥቀስ እንዳብራሩት በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎችና የመምህሩ ሚና ከፍተኛ ነው።ይህ ሚና በትምህርት ባለሙያዎች አጠራር ማቀናጀት፣ መስተጋብር፣ ተሳትፎ፣ ሂደትና አተገባበር ሞዴል በመባል ይታወቃሉ በማለት ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ በተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ መምህሩና ተማሪዎቹ ኃለፊነትን፣ ውሳኔ ሰጭነትንና እርስ በርስ መከባበርን ይጋራሉ። ዲሞክራሲያዊ በሆነ ዘመናዊ

መወሰን፣ መተግበርና የምዘና ሂደቶችን ውሳኔም ሳይቀር ከመምህራን ጋር በመተባበር ያከናውናሉ፤ ከትምህርት ምንጭ ጋር መስተጋብር ይፈጥራሉ፤ በከፍተኛ ደረጃ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ የትምህርት ክንውኖችን ይተገብራሉ።የየስራ ድርሻቸውን ተረድተው የተጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣትና የታቀደውን ዓላማ በጥሩ ሁኔታ ለማጠናቀቅ የሚተገበት አሳታፊ የሆነ የትምህርት አተገባበር ዘዴ ነው።

2.1.6 በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ የቡድን ማስተማር ዘዴ

እንደ Abraham et al. (1999) አገላለጽ በዘመናዊ ትምህርት አሰጣጥ ሂደት ማስተማር በጣም ጠቃሚ የሚሆነው ተማሪዎች በመምህራቸው የሚተላለፈውን ዕውቀት ብቻ ከመጠበቅ ይልቅ በራሳቸው ጥረት በንቃት እንዲሳተፉ፣ እንዲመራመሩ፣ እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩ፣ እንዲጠይቁ፣ የዳበረ ክሂሎት እንዲያጎለብቱ ማድረግ ሲቻል ነው።

በተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ተማሪዎችን በንቃት የሚያሳትፉ ዘዴዎች በርካታ ናቸው። O'Neill and McMahon (2005)፣ Lue (2000)፣ Plass (1998)፣ Aggrawal (1996)፣Tudor(1996) እና በሌሎችም ድርሳናት የተለያዩ የአቀራረብ መገለጫዎችን፤ የቡድን ማስተማር ዘዴ፣ችግር ፈች ዘዴ፣ትብብራዊ ዘዴ፣በራስ የመማር ዘዴ፣ሚና ነጠቃ ዘዴ፣ወዘተ. በማለት ይዘረዝራሉ።ይሁን እንጂ የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ትኩረት የቡድን ማስተማር ዘዴ ስለሆነ ቀጥሎ ይቀርባል።

2.1.6.1 የቡድን ማስተማር ዘዴ ምንነት

የቡድን ማስተማር ዘዴ በመማር-ማስተማር ሂደት የታወቀው ከ1930 ዓ/ም ወዲህ ሲሆን ዘዴው ተማሪዎችን በቡድን አደራጅቶ በአንድ በተወሰነ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንዲወያዩ፣ እንዲመራመሩ፣ እንዲጠይቁና እየተረዳዱ እንዲማሩ፣በመጨረሻም ወደ አንድ ውሳኔ እንዲደርሱ የሚደረግበት የማስተማር ዘዴ ነው (ማረው፣1987፡91)።

መለሰ (1988፣18) እንዳብራሩት፣የቡድን ማስተማር ዘዴ በርከት ያሉ ሰዎች በአንድ በተወሰነ ጉዳይ ላይ በቃል ሐሳብ እየተለዋወጡ የሚማሩበት መንገድ ነው።በጋራ ለአንድ ጥያቄ መልስ ለመፈለግ ሐሳብ የሚንሸራሸርበት፣ለጋራ ችግር የጋራ መፍትሔ ለመሻት ክርክር የሚደረግበት መድረክ ነው።

Abraham et al. (1999፣90) እንዳስረዱት፣ ውጤታማ የሚባለው የቡድን ማስተማር ዘዴ የሚደራጀው በመምህሩ አማካይነት ነው።መምህሩ ተማሪዎችን ከአምስት እስከ ሰባት ባልበለጡ አባላት አደራጅቶ እርስ በርሳቸው እንዲወያዩ በማድረግ ግልጽ ያልሆነላቸውን ሐሳብ በቀላሉ እንዲገነዘቡ ያደርጋል።

2.1.6.2 የቡድን ማስተማር ዘዴ ጠቀሜታ

የቡድን ማስተማር ዘዴ ተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ዘዴ በሚከተል ክፍል ውስጥ በጣም ጠቃሚ ከሚባሉ የማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ ነው።ዘዴው ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በማበረታታትና የእርስ በርስ ግንኙነትን በማሳደግ የትምህርቱ ውጤት እንዲሻሻል፣ተግባቦታዊ ክሂሎት እንዲዳብር፣በጋራ የመስራት ባህል እንዲጎለብት፣የመማር ተነሳሶት እንዲጨምር፣ ወዘተ. ጠቀሜታ አለው (O'Neilland Tim Mcmahon 2005)።

እንደ SilberMan (1994)፣ McGreal (1989) እና LittleJohn (1987) አገላለጽ፣ የቡድን ማስተማር ዘዴ በቋንቋ ትምህርትም ሆነ በሌሎች ትምህርት ዘርፎች ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው።በተለይ የተማሪ ቁጥር በበዛበት ክፍል ውስጥ መምህሩ በአግባቡ ለማስተናገድና ተገቢውን እገዛ ለማድረግ ሊቸገር ይችላል። ለዚህም የቡድን ማስተማር ዘዴ ሁሉንም ተማሪዎች በትምህርት ክንውን ውስጥ በንቃት በማሳተፍና ትምህርቱን እንዲከታተሉ በማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ነው።ምክንያቱም የተማሪውን ክንውን ተከታትሎ እገዛ ለማድረግ ምቹ በመሆኑ ነው።

Light and Roycox (2001:117)፣Abraham etal. (1996:26)፣Silberman (1996:13)፣ Long and Porter (1985:33)፣ እና በድሩ (1990:37) የቡድን የማስተማር ዘዴ በጥንቃቄ ከታቀደና ተግባራዊ ከሆነ ለተማሪዎች ሊያስገኝ የሚችለውን ጠቀሜታ አስመልክተው ያነሷቸው ነጥቦች ተጠቃልለው እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

- በክፍል ውስጥ ማራኪ የሆነ የመማር-ማስተማር ሂደት እንዲፈጠር ከማስቻሉ ባሻገር ትምህርታዊ ተሳትፏቸው እንዲጨምር ያደርጋል።
- ሁሉንም ተማሪዎች ባሳተፈ መልኩ ተባብረውና ተደጋግፈው በመስራት ችግሮችን በራሳቸው የመፍታት ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ያስችላል።
- አንድን ሃሳብ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለመረዳት በጥልቀት ማሰብን፣ መተንተንን፣መገምገምን፣ማስረጃ ማቅረብን፣ተጠየቃዊ ምክንያት መስጠትን፣ ሃሳቦችን ማዛመድን፣ሂሳዊ አስተሳሰብ ማራመድን በማጎልበት የዕውቀትና የክሂሎት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ያደርጋል።
- ተማሪዎች እርስ በርስ በመወያየት እና በመረዳዳት ሐሳብ የመግለጽ አቅማቸውንና ሌሎችን የማዳመጥ ችሎታቸውን በማዳበር ስብእናቸውን ለማጠናከር ይረዳል።

- ውይይት፣ክርክር፣ገለጻ በማድረግ ሃሳብ የማንሸራሸር ችሎታን ያዳብራል።
- በክፍል ጓደኞቻቸው ፊት ወጥተው በተዳጋገሚ ጊዜ እንዲናገሩ እድል የሚሰጥ በመሆኑ በራስ የመተማመን ችሎታን ያዳብራል።
- በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ጤናማ መስተጋብር እንዲኖር ያደርጋል።
- ዓይናፋር ተማሪዎች ከሰው ፊት መናገር እንዲችሉ ያበረታታል።
- በግል ለመስራት የሚያስቸግሩ ተግባራትን በትብብር ለመስራት ያስችላል።

2.1.6.3 የቡድን ማደራጃ መንገዶች

ቡድን ለማደራጀት ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ካለባቸው ጉዳዮች መካከል የተለያዩ ምሁራን የሚከተሉትን ነጥቦች ዘርዝረዋል፤

ችሎታ፣ አንድ ቡድን በተመሳሳይ ወይም በቅይጥ ቡድን ሊደራጅ ይችላል።ይሁን እንጂ የተለያየ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ቀላቅሎ በአንድ ቡድን መመደብ በተለይም ለደካማ ተማሪዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።ምክንያቱም ደካማው ከጠንካራው ተማሪ ግልጽ ያልሆነለትን ነገር ሲማር ጠንካራውም ባስተማረው ቁጥር ለራሱም የበለጠ እየተረዳ ይሄዳል (Harmer 1991፣Farrant 1980)።

ጾታ፣ በቡድን ምደባ ጊዜ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ጾታ ነው።ምክንያቱም ወንድና ሴት ተማሪዎች እህታዊና ወንድማዊ ስሜት አድሮባቸው በትምህርታዊ ጉዳዮች መወያየትና መረዳዳት እንዲችሉ ማድረግ ነው።ይሁን እንጂ በቡድን አደረጃጀት ጊዜ ከጾታ ይልቅ ለችሎታ ቅየጣ የበለጠ ትኩረት ቢሰጥ የቡድን ማስተማር ዓላማን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል Farrant (1980) ይገልጻሉ።

የቡድን ስራ ክንውን ተለዋወጭ በመሆኑ በአንድ ቡድን ውስጥ የሚዋቀሩት ተማሪዎች ቁጥር በየጊዜው ሊለያይ ይችላል።ነገር ግን በአንድ ቡድን ውስጥ ሊካተቱ

የሚገባቸው ተማሪዎች በጋራ የሚሰጣቸውን ሥራ መሰረት በማድረግ በጥንድና ከጥንድ በላይ በሆነ መንገድ ቡድን እንዲመሰርቱ ማድረግ ይቻላል (Cross፡1995)::

የአንድ ቡድን አባላት ቁጥርን በተመለከተ እንደ ሥራው ዓይነትና ባህርይ ሊወሰን እንደሚችል በመጥቀስ የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ሃሳብ ሰንዝረዋል። ለውጤታማ የቡድን ማስተማር ተግባር የአባላቱ ቁጥር Siberman (1996) ከአምስት እስከ ስምንት፣ Cross (1995) ቢያንስ አራት ቢበዛ ስደስት፣ Doff (1988) ከአራት እስከ አምስት፣ McGreal (1988) ከአራት እስከ አምስት፣ Byrne (1992) ከአራት እስከ ስምንት ፣ ለማ (1998) ከሶስት እስከ ስድስት፣ መለሰ (1988) ከአራት አስከ አምስት፣ በድሩ(1990) ከአምስት እስከ አስር ሊሆን ይችላል በማለት ገልጸዋል።በተጨማሪም ማረው (1987) እና ደረጀ (1999) በአንድ ቡድን ውስጥ የአባላት ቁጥር አነስተኛ ቢሆን ይመረጣል።ምክንያቱም በውይይት ጊዜ የሐሳብ ልዩነትን አበላልጦ ወደ አንድ ውሳኔ ለማድረስ እንዲቻል፣ ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ለማድረግና ተሳትፏቸውን ለመቆጣጠር አመቺነት እንዳለው ገልጸዋል።

እንደ Silberman (1996፡112) አገላለጽም፣በቡድን ውስጥ የሚዋቀሩት ተማሪዎች ቁጥር ከአምስት ካነሰ የተለያዩ ሓሳቦችንና አመለካከቶችን የማግኘት እንዲሁም ጥሩ የእርስ በርስ ግንኙነት የመፍጠር ሂደት ደካማ ይሆናል።በሌላ በኩል ቁጥሩ ከስምንት ከበለጠ ደግሞ እያንዳንዱ የቡድን አባላት እኩል የመሳተፍ ዕድላቸው እየቀነሰ ይሄዳል በማለት ያስረዳሉ።

2.1.6.4 በቡድን ማስተማር ዘዴ የመምህሩ ተግባር

የቡድን ማስተማር ዘዴ የተማሪዎቹ በየቡድን ውስጥ ተዋቅረው መገኘታቸው ብቻውን የቡድን የማስተማር ዘዴን ውጤታማ አያደርገውም፤

ማንኛውም የቡድን ስራ ውጤታማ እንዲሆን የሚያደርጉ ቁልፍ የመምህሩ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው (Abraham etal.1990)፤

- የቡድን ሥራው ዓላማ ለተማሪዎች በግልጽ ሊነገራቸው ይገባል።መምህሩ በከፍተኛ ሁኔታ በማቀድ ከተማሪዎች ጋር ተቀራርቦና ተግባብቶ የቡድን ሥራውን ዓላማ መግለጽ ይጠበቅበታል።በተጨማሪ ክንውኑ የማውጣጣትና ፈልጎ የማግኘት ክሂልንና ሂሳዊ አስተሳሰብን የሚያነቃቃ መሆን አለበት።
- የቡድን ሥራው ትዕዛዝ ግልጽ መሆን አለበት።የቡድን ሥራውን የሚሰሩት ተማሪዎች ምን እንደሚሰሩ፣ሥራውን ሰርቶ ለማጠናቀቅ ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅና በቡድን ሥራው ማጠናቀቂያ ምን ግኝት ማፍለቅ ወይም ማንጸባረቅ እንደሚገባቸው ሊያውቁ ይገባል።
- ተማሪዎች የቡድን ሥራውን በክፍል ውስጥ በሚሰሩበት ጊዜ መምህሩ ፈጣን መሆን አለበት።መምህሩ በክፍል ውስጥ እየተዘዋወረ በንቃት እየተከታተለ በተዋቀሩት ቡድኖች ውስጥ ያሉት ተማሪዎች በሙሉ በንቃት የሚሳተፉ መሆን አለመሆናቸውን በመቆጣጠር ሁኔታዎችን በማመቻቸትና በመርዳት ተማሪዎቹ የተሰጣቸውን ሥራ እንዲጨርሱ ማድረግ አለበት።ምክንያቱም መምህሩ ለተማሪዎች ቅርብ በሆነ ቁጥር የተማሪዎች የመሥራት ፍላጎት ይጨምራል።
- ሁሉም ተዋቃሪ ቡድኖች ተመሳሳይ ሥራ እንዲሰሩ አይጠበቅም።የተዋጣ የቡድን ሥራ እንዲኖር በአብዛኛው በቡድን ሥራ ክንውን ወቅት ቡድኖች

የተለያየ ስራ እንዲሰሩ በማድረግ እያንዳንዱ ቡድን በመጨረሻ የደረሰበትን ድምዳሜ ለተቀሩ የክፍል አጋሮቹ እንዲያቀርብ ማድረግ ነው።በዚህ ወቅት ተማሪዎች በትክክል መረጃዎችን እንዲለዋወጡ ዕድል ያገኛሉ።ይህም የተማሪዎችን የተግባቦት ክሂል እና በራስ የመተማመን አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ያስችላቸዋል።

- ቡድኖችን በተለያየ መንገድ በመመስረት እንዲሳተፉ ማድረግ።በተሰጠው ሥራ መሰረት ቡድኖችን ብልሃት በተሞላበት መንገድ መመስረት ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው።የሚመሰረቱት ቡድኖች ተማሪዎች አጠገብ ለአጠገብ መቀመጣቸውን መሰረት አድርጎ መደራጀት በጾታ፣በችሎታ፣በፍላጎት፣በራስ ምርጫ፣ወይም ዘፈቀዳዊ ምርጫን መሰረት አድርጎ ሊሆን ይችላል።

እንደ Grafield (1993፡15) እና Lue (2000:14) አገላለጽ፣ አንድን ቡድን ተማሪዎች በፍላጎታቸው እንዲመርጡ በማድረግ ወይም መምህራን ተመሳሳይነት /Homogenity/ ወይም ቅይጥነትን /Hetrogenity/ መስፈርት አድርገው ተማሪዎችን በመምረጥ ማደራጀት ይችላሉ። ነገር ግን በተመሳሳይነት መስፈርት ከሚደራጁ ቡድኖች በቅይጥነት መስፈርት የሚደራጁ ቡድኖች ለመማር ማስተማር ሂደት ጠቃሚና ውጤታማ ናቸው። ምክንያቱም የተለያየ ዳራ፣ጾታና ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች በጋራ ሥራ እኩል እንዲሳተፉ ያደርጋቸዋል።

2.1.6.5 የቡድን ማስተማር ዘዴ ጠንካራ ጎኖች

የቡድን ማስተማር ዘዴ ጠንካራ ጎኖችን በተመለከተ ማረው (1987)፣ደባሱ (1990) እና መለሰ (1988) እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፤

- ሓሳቦችንና ልምዶችን ለማፍለቅና ግልጽ ለማድረግ ያመቻል።
- በአንድ ሃሳብ በሰፊው ለመወያየት ያስችላል።
- ሁሉም ተማሪዎች የመሳተፍ ዕድል ያገኛሉ።
- ተማሪዎች የመተባበርን፣ ለችግሮች መፍትሄ የማፈላለግን፣ በሳል አስተያየት መስጠትን፣ ወዘተ. ክሂሎት እንዲያዳብሩ ይረዳል።
- በተሳታፊዎች መካከል የሚቀርቡ የሐሳብ ልዩነቶችን በማቻቻል እተፈለገው ውጤት ላይ ለመድረስ ያስችላል።
- ተማሪዎች የሌሎችን ሃሳብና አመለካከት የሚያከብሩና ራሳቸውም የተሰማቸውን መግለጽ የሚችሉ ጠንካራ ስብዕና ያላቸው እንዲሆኑ ያበረታታል።
- ጥሩ መሪ ለመሆን እምቅ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎችን በመምረጥና በመለየት እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ለመርዳት ያስችላል።
- ሁሉንም ተማሪዎች በማበረታታት የተግባቦት ችልታቸውን እንዲያጎለብቱ ዕድል ይሰጣል (Lue 2000፣ Grafield 1993)።

2.1.6.6 የቡድን ማስተማር ዘዴ ደካማ ጎኖች

ተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዘዴ በሚከተል ክፍል ውስጥ የቡድን ማስተማር ዘዴ በጣም ጠቃሚ ቢሆንም በጥንቃቄ ካልተያዘ የተወሰኑ ደካማ ጎኖች ይኖሩታል(Doff 1988)፤

- ተማሪዎች በሚሳተፉባቸው ቡድኖች ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት የአባላት ቁጥር ከበዛ ለአያያዝና ለአመራር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡
- የቡድን ውይይቱ በጥቂት ተማሪዎች የበላይነት ቁጥጥር ስር ሊወድቅ ይችላል፡፡
- በቡድን ሥራ ጊዜ የሚሰማው ድምጽ በቅርብ ያሉ ክፍል ተማሪዎችን ይረብሻል፡፡
- ተማሪዎች ስህተት እንዲሰሩ ይጋብዛል፡፡
- ተሳትፎ የማያደርጉ ተማሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡
- የታቀደውን ይዘት በወቅቱ ለማጠናቀቅ ሰፊ ጊዜ ይወስዳል፡፡

በአጠቃላይ የቡድን ማስተማር ዘዴ ተማሪዎች ነጻነት እንዲሰማቸው በማድረግ እርስ በርሳቸው በአንክሮ አንዲደማመጡ፣እንዲወያዩ፣ምክንያታዊ ሆነው እንዲከራከሩ፣ ጠቃሚ ሐሳቦችን እንዲያራምዱ፣ሂሳዊ አስተሳሰብ በማዳበር በቋንቋው በሚገባ ተጠቅመው የተግባቦት ችሎታቸውን ለማጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

2.1.7 የመማሪያ ክፍሎች አደረጃጀትና የተማሪዎች አቀማመጥ

እንደ Barbara, etal. (1995፡203) በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ የክፍል ውስጥ አወቃቀርና የተማሪዎች አቀማመጥ በመማር-ማስተማር ክንውኑ ላይ አስተዋጽኦ አለው። የተማሪዎች አቀማመጥና የመማሪያ ክፍል አደረጃጀት ለተማሪው ብቻ ሳይሆን መምህራን ከቦታ ቦታ በቀላሉ እየተንቀሳቀሱ ተማሪዎቻቸው በትምህርታቸው እንዳይሰላቹና ለመማር ያላቸው ፍላጎት በየጊዜው እንዲነሳሳ ለማበረታታት፣ለመከታተል፣ለመቆጣጠር ያስችላቸዋል፤ ጥሩ የክፍል አደረጃጀትና ምቹ የተማሪዎች አቀማመጥ ሲኖር መማር-ማስተማር ሂደቱም ውጤታማ እንደሚሆን Lue (2000፡12) ይገልጻሉ።

Barbara, etal.(1995፡203) ሲገልጹ፣የተማሪዎች አቀማመጥና የክፍል ስፋት የተማሪዎችን ትምህርት የሚያነቃቃ፣በቅርበት እርስ በርስ እየተረዳዱ እንዲሰሩ የሚያደርግ፣ተለዋዋጭና ተመራጭ መሆን እንዳለበት ይገልጻሉ።

2.1.8 በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የምዘና ስልት

ምዘና ተማሪዎች "ምን ያውቃሉ?" ወይም "ምን ተገንዝበዋል?" የሚለውን ለመረዳት በብዙ አቅጣጫ መረጃ መሰብሰቢያ ሂደት ነው እንጂ ለተማሪዎች ነጥብ በመስጠት ደረጃ ማውጣት ወይም ማበላለጥ፣ ማሳለፍና መጣልን ለመፍጠር አይደለም (Thomas etal. 2006:131)።

O'Neill and McMahon (2005) Black (1999)ን በመጥቀስ እንደገለጹት፣ ቀደም ሲል በስፋት አገልግሎት ይሰጥ የነበረው ባሕላዊ የማስተማር ዘዴ የበለጠ ትኩረቱ ማርክ መስጠትና ደረጃ ማውጣት ላይ ነው።ተማሪዎች ትምህርታቸው ላይ ተግተው እንዲሰሩና በሂደት ውጤት እንዲያስመዘግቡ ከማድረግ ይልቅ መፈተን፣ማወዳደርና ማበላለጥ ላይ ያተኩራል።

በዘዴው የሚካሄደው ምዘና ተማሪዎች እርስ በርስ ፉክክርና ውድድር በማድረግ አንዱ አንዱን መጣል ላይ የተመሰረተ እንጂ ግላዊ ስብእናን ማሳደግ ላይ ያተኮረ አይደለም።የተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ምዘና ዋነኛ ትኩረቱ ተማሪዎች በክፍልም ከክፍል ውጭ ያገኙትን ዕውቀት፣ ክሂሎትና ልምድ በአግባቡ መጨበጣቸውን፣ ነገሮችን ከተለያየ አቅጣጫ መመዘን መቻላቸውን፣የትምህርት አቀባበል ስልትና ብቃታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መረጃዎችን በመሰብሰብና ጥንካሬና ድክመታቸውን በመለየት ማገዝ እንዲያስችል ነው።

Thomas etal. (2006:132) በበኩላቸው ምዘና አስተሳሰብን የሚያጎለብት፣እይታን የሚያሰፋ፣ጠልቆ ማሰብን የሚያበረታታ መሆን እንዳለበት ይገልጻሉ።

O'Neill and Mcmahon (2005) በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ተከታታይ ምዘና ማድረግ ተማሪዎች ለትምህርቱ የበለጠ እንዲተጉ፣ ያሉበትን ደረጃ እንዲያውቁ፣ከራሳቸውና ከቢጤዎቻቸው ጋር ምዘና እንዲያካሂዱ፣እርስ በርስ በመገማገም፣ በመተራረም በራስ መተማመንን እንዲያጎለብቱ ያግዛል።በተጨማሪ መምህራን ተማሪዎቻቸው ያለባቸውን ደካማና ጠንካራ ጎን በመፈተሽ እገዛ መስጠት እንዲችሉ፣ ምቹ የሆኑ የማስተማሪያ ስልቶችንና ቁሳቁሶችን እንዲመርጡ፣ በመማር-ማስተማር ሂደት መሻሻል ስለሚገባቸው ሁኔታዎች አቅጣጫ እንዲጠቁሟቸው በአጠቃላይ የትምህርቱ መርሃ ግብር ስለ መተግበሩ ምጋቤ ምላሽ ለማግኘት ይጠቅማል።

2.1.9 ተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ሁኔታዎች፤

ተማሪ-ተኮር የትምህርት አቀራረብ ዘዴን ተግባራዊ ለማድረግ አደናቃፊ የሚሆኑ ሁኔታዎችን በተመለከተ Lue (2000:9) ከሰው ጋር በቀጥታ የሚገናኙ እና በቀጥታ ከሰው ጋር የማይገናኙ ሁኔታዎች ሲሆኑ በውስጣቸው ከግለሰቦች ባህርይ፣ ከትምህርት ስልጠና፣ ከትምህርት መሳሪያ፣ ከስብዕናና ከአካባቢ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ገጽታዎችን እንደሚያንጸባርቁ ይገልጻሉ።

McMahon (2005)፣Tudor (1996) እና Nunan (1988) ከሰው ጋር በቀጥተኛ የተገናኙ ዘዴውን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ሁኔታዎች፤

- የመምህራን ቅድመ አገልግሎትና በአገልግሎት ወቅት በቂ ስልጠና አለማግኘት፣
- መምህራን በዘዴው ተጠቅመው ለማስተማር ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ መሆን፤
- የተማሪዎች ዕውቀትና ፍላጎት አነስተኛ መሆን፤
- የትምህርት ሃላፊዎች ዕውቀት፣ ፍላጎትና በዘዴው ላይ ያላቸው የተዛባ አመለካከት፤
- የትምህርት ሱፐር ቫየዘሮች ክትትልና እገዛ ማነስ እና ሰዎች አዲስ ነገር ለመቀበል ያላቸው ዝግጁነት ዝቅተኛ መሆን ናቸው በማለት አብራርተዋል።

ከሰው ጋር በቀጥታ የማይገናኙ ሁኔታዎችን በተመለከተም የማስተማሪያ መሳሪያዎች ዘዴውን ተግባራዊ ለማድረግ ያላቸው ብቃት ማነስ እና የትምህርት ቤት አካላዊና አካባቢያዊ ምቾት መጓደል እንደሆነም ተጠቅሷል።

2.1.10 የጽሕፈት ክሂል

2.1.10 .1 የጽሕፈት ክሂል ምንነት

የጽሕፈት ትምህርት ምንነትን በተመለከት በተለያዩ ምሁራን የተገለጹ ሀሳቦችን እናገኛለን፤ ከነዚሁ መካከል Widdowson (1987፣57)፣Harmer (1991፣16) እና Raimes (1983፣5) ጽሕፈት በእይታዊ ምልክቶች በመታገዝ ሰዎች ሀሳብ የሚለዋወጡበትና የእርስ በርስ መስተጋብር የሚመሰርቱበት ተግባቦታዊ መሳሪያ ነው። በመተላለፊያ ስልቱም እይታዊ፣በትግበራዊ አፍላቂ፣በተግባቦታዊ ባህርይው ደግሞ ርቱዕ ክሂል እንደሆነ ገልጸዋል።

ጽሕፈት በተግባቦታዊ መሳሪያነቱ የተገኘን ዕውቀት ማስተላለፊያ ብቻ ሳይሆን መረጃን ማቀበያ በእይታዊ ምልክቶች ቀርጾ ማቆያ መንገድ ነው። ስለዚህም ጽሕፈት ገጠመኞችን ለመመዝገብ፣የተለያዩ ጽሑፎችን (ደብዳቤ፣ዘገባ፣ማስታወሻ) ለመጻፍ፣ ለማሰብ፣ለመማር የሚረዳ የቋንቋ ትምህርት መሰረታዊ ክሂል ነው (Troyka 1990፣2፤Hedge (1988፣5)።

ጽሕፈት በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ሆሄያትን ከድምጾች ጋር በማያያዝ የቋንቋን ህግ ተከትሎ በወረቀት ላይ በማስፈር ሀሳብ የሚገለጽበት ሂደት ነው።ይሁን እንጂ ጽሕፈት ሆሄያትን አቀናጅቶ ከማስቀመጥ ባሻገር አካልና አእምሮን በማቀናጀት ሀሳብን በጽሑፍ መልክ የማቀናበር ተግባር ነው።

እንደ Rivers (1981፣291-294) እና Nunan (1989፣36) አገላለጽ፣ማንኛውም ሰው በአንድ ቋንቋ እንደ'ት መጻፍ እንዳለበት ለማወቅ የግድ መማር ይኖርበታል።

Raimes (1983፣14) በበኩላቸው፣ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁና እረስ በርስ ቁርኝት ያላቸው ዐረፍተ ነገሮችን በማመንጨት ሀሳብን በጽሑፍ መግለጽ የሚያስችል ክሂል እንደሆነ ያስረዳሉ።

Nunan (1989፣36) Bell and Burnaby (1984)ን ጠቅሰው የጽሕፈት ክሂል በአንድ ጊዜ የጽሑፉን ይዘት፣የአጻጻፍ ስልቱን፣የዐረፍተ ነገር አወቃቀሩን፣የቃላት ምርጫን፣ስርዓተ ነጥብን፣የሀሳብ አንድነትን፣ ግጥምጥምነትን፣ ተከታታይነትን፣ ወዘተ. ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን ከማሰብ ጋር የተያያዘ ውስብስብ ተግባር እንደሆነ ገልጸዋል።

2.1.10.2 የጽሕፈት ትምህርት ዓላማ

የጽሕፈት ትምህርት ተቀዳሚ ዓላማ ተማሪዎች በጸሑፍ አማካይነት ሀሳባቸውን በተቃና መንገድ በመግለጽ ጽሑፋዊ ተግባቦትን እንዲለማመዱ ማስቻል[1] እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ።

እንደ Raimes (1983፣4-7) ገለጻ፣ተማሪዎች ጽሕፈትን የሚማሩባቸው ዓላማዎች ዐረፍተ ነገርን ከመጻፍ በዘለለ መልኩ ሊታዩ ይገባቸዋል በማለት ዓላማዎቹ የሚያካትታቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ይዘረዝራሉ።እነሱም ከአንባቢ ጋር ለመግባባት፣ከገጽ ለገጽ ተራክቦ ውጭ[2] ሀሳብን በጽሑፍ ለመግለጽ፣ዕውቀት ለማግኘት፣በዕለት ተዕለት የሕይወት ገጠመኞች የሚታዩ ክስተቶችን መዝግቦ ሰማቆየትና በቋንቋው የሚጻፉ የጽሑፍ ስራዎች ለተማሪዎች እንግዳ እንዳይሆኑ ማስቻል ናቸው።

በተጨማሪም ምሁሩ ጽሕፈትን መማር ሁለት ዓላማዎች እንዳሉት ያስረዳሉ።አንደኛው ጽሕፈትን በግብነት በማስተማር የጸሐፍ ተግባቦታዊ ክሂሎት፣ርቱዕነት (fluency) እና ትክክለኛነት (accuracy) ማለማመድ ሲሆን ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ የታላሚውን ቋንቋ ስነ ልሳናዊ ክፍሎች ማለትም የቃላት፣የሰዋስው፣ወዘተ.ችሎታ ማስተማር ነው።

እንደ Brandy (1994፣135) አገላለጽ የጽሕፈት ትምህርት ዓላማ ከግለሰባዊና ማሕበረሰባዊ ጠቀሜታው አኳያም ሊታይ ይችላል።ጽሕፈትን መማር ለግለሰቡ አመለካከቱን ለመግለጽና ለመደገፍ፣አእምሯዊ ተግባራትን ለማከናወንና የተጻፉ ሰነዶችን ለመመርመር ሲያግዘው፣ ለማሕበረሰቡም የጽሑፍ ቋንቋ ቅርጽ ለመያዝ፣የስነ ጽሑፍ ስራዎችን ልዩ ልዩ መረጃዎች ለማጠናቀር ያገለግላል።

Heaton (1991፣135) በበኩላቸው ጽሕፈትን መማር የተለያዩ የጽሕፈት ንኡሳን ክሂሎችን (ተገቢነት ያላቸው አረፍተ ነገሮች የመጻፍ፣ስርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ ለአገልግሎት የማዋል፣ተቀባይነት ያለው ሐሳብ የመምረጥ፣የማንጨትና አስፋፍቶ የማቅረብ፣ተፈላጊውን ሀሳብ ለማስተላለፍ ተገቢ የሆኑ የአጻጻፍ ስልቶችን የመምረጥ፣የዐረፍተ ነገርና የአንቀጽ አወቃቀር ስርዓትን ጠብቆ የመጻፍ፣የተለመደና ሰዋሰዋዊ ቋንቋን የመጠቀም፣ወዘተ.) ለማዳበር ይረዳል ይላሉ።

ጠቅለል ባለ አገላለጽ የጽሕፈት ትምህርት ዓለማዎች የተማሪዎችን የቃላትና የሰዋስው ዕውቀትን በማጠናከር በጽሑፍ አማካይነት እንዲግባቡ ማስቻል፣ የተለያዩ የጽሕፈት ንኡሳን ክሂሎችን ማለማመድ፣ ወዘተ. ናቸው።ከዚህ ባሻገር የመማሩ ዓላማ ግለሰባዊና ማሕበረሰባዊ ጠቀሜታ ማስገኘቱ እና ለጽሑፍ ተግባቦት አስፈላጊ የሆኑትን ክሂሎች ለማዳበር ማገዙ ተጠቃሽ ነጥቦች ሲሆኑ ይህን ተግባራዊ ለማድረግም በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ የሚሰሩ የጽሕፈት ትምህርት ተግባራት ድርሻቸው ጉልህ ነው።

የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች ከታላሚው ቋንቋ የሚጠበቁትን ክሂሎችና ዕውቀቶች ማስጨበጥ ነው።

የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎችም የራሳቸው የሆኑ ዓላማዎች እንዳሉ የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ።Attkins (1996፣114) የመጻፍ ክሂል መልመጃ ሁለት ዓላማዎች እንዳሉት ይገልጻሉ።አንደኛው ዓላማ የተማሪዎችን የቋንቋ ዕውቀት ማለትም የቃላትና የሰዋስው ችሎታ ማጠናከር ሲሆን ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ ተማሪዎች ተግባቦታዊ የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው።

በአጠቃላይ የጽሕፈት ትምህርት መልመጃዎች ዓላማ የተማሪዎችን የቃላትና የሰዋስው ዕውቀትን በማጠናከር በጽሑፍ አማካይነት እንዲግባቡ ማስቻል ነው።ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር መግለጽ እንደሚችሉ ሁሉ በአእምሯቸው የሚመላለሱትን ሀሳቦች በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታቸው መዳበር አለበት።ይህም ከሚያዳምጡትና ከሚያነቡት ተነስተው ለግንዛቤ የሚረዳቸውን ሀሳብ መዝግቦ ለመያዝ ይጠቅማቸዋል።በሂደቱም የቋንቋውን ምልክቶች ከመለየት ባሻገር ሰዋስዋዊ ስርዓቱን እንዲያውቁት ያግዛቸዋል።

2.1.10.3 የጽሕፈትን ትምህርት አስቸጋሪ የሚያደርጉ ሁኔታዎች

የጽሕፈትን ትምህርት ዓላማ በቀላሉ ከግብ ለማድረስ አስቸጋሪ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መኖራቸውን የተላያዩ ምሁራን ይገልጻሉ። ከነዚህም Barr እና Barbara (1997፣17) አገላለጽ፣ጽሕፈት ባሉት ባህርያቱ ውስብስብና በቀላሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊዳብር የሚችል ክሂል ባለመሆኑ ብዙ ጊዜ ወስዶ ልምምድ ማድረግ የሚጠይቅ ነው።

ጽሕፈትን አስቸጋሪ እንዲሆን የሚያደረጉ ባህርያት፡- ስነልቦናዊ፣ ስነልሳናዊ እና አእምሯዊ ገጽታዎቹ ናቸው Hedge (19887)፣Pincas (1982፣18)፣ Raimes (1983፣11)።

ሀ. ስነልቦናዊ ባህርይ

በጽሕፈት ክሂል መማር-ማስተማር ሂደት ወቅት አንባቢውን ማሰብ የማይቀር ጉዳይ ነው።መልእክቱ ለአንባቢው በትክክል እንዲደርሰው ለማድረግም ደግሞ ጸሓፊው በሓሳብ መውጣት መውረድ ስላለበት ይጨነቃል። "የጽሕፈት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች ቁና ቁና የመተንፈሻ፣እግራቸውን የማፋተጊያና እርሳሳቸውን ማኘኪያ የስቃይ ጊዜ ነው።" በማለት ጽሕፈት ምን ያህል ፈታኝ እንደሆነ Hedge (1988፣5) ይገልጻሉ።ከዚህ ሓሳብ በመነሳትም የጽህፈት ክሂል ውስጣዊ ጭንቀት የሚፈጥር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ለ. ስነልሳናዊ ባህርይ

ስነልሳን ቋንቋ የሚጠናበት ሳይንስ በመሆኑ የአንድ ቋንቋ ውስጣዊና ውጫዊ ገጽታው ይጠናበታል።በጽሕፈት ትምህርት ረገድም የስነልሳን ዕውቀት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ምክንያቱም ሀሳብን በጽሕፈት አማካይነት በትክክል ለመግለጽ የቋንቋውን ስርዓት ጠንቅቆ ማወቅ የግድ ስለሆነ ነው።ይህንንም ዕውቀት ለማዳበር በንግግር ወቅት ትኩረት የማናደርግባቸው ነገር ግን በጽሕፈት ጊዜ የሚተኮርባቸው ነገሮች መኖራቸውን ማስተዋል ይገባል (Hedge 1988፣19)።

ጽሕፈት በከፍተኛ ደረጃ የአእምሮ እንቅስቃሴ (በሀሳብ መውጣ መውረድ) የሚጠይቅ ትምህርት ነው።የጽሑፍ ስራ የግንዛቤን መዳበር ይጠይቃል።Moore (1995፣13) "መጻፍ ማለት ማሰብ ማለት ነው።" በማለት ሳይተሰብበት የሚከናወን የጽሕፈት ተግባር አለመኖሩን ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ የጽሕፈትን ትምህርት አስቻጋሪ ከሚያደርጉ ሁኔታዎች በመነሳት ክሂሉን ለማስተማር ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግን የሚጠይቁ ነገሮች እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል።የተማሪዎችን የስነልቦና ሁኔታ በቋንቋው ያላቸውን የዕውቀት ደረጃና የአእምሮ ብስለታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለክሂሉ መዳበር የሚቀርቡትን ይዘቶች ተገቢ በሆነ ስነ ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

2.1.10.4 የጽሕፈት ክሂልን የማቀድና የማስተመማር መርሆች

ተማሪዎች በጽሑፍ አማካይነት ሀሳባቸውን በተገቢ ሁኔታ የመግለጽ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ለማድረግ መምህሩ የጽሕፈትን ክሂል በሚያዳብሩና የሰዋስውና የቃላት ችሎታን በሚያጠናክሩ መልመጃዎች ላይ በማተኮር ትምህቱን ማቅረብ እና በትግበራ ሂደቱም የሚከተሉትን መርሆች ማስታወስ ተገቢ ነው (Attkins 1996፣11)፤

- የመጻፍ ክሂል በክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ የሚለማመዱበት መሆን አለበት።በክፍል ውስጥ የሚመደበው ክፍለ ጊዜ ለሰዋስውና ለቃላት ትምህርት ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች መልመጃዎችን በመስራት የጽሑፍ ክሂላቸውን ማዳበር አለባቸው።
- በክፍል ውስጥ የሚተገበሩት መልመጃዎችም አስደሳችና ለመጻፍ የሚያነሳሱ፣ዓላማ ያላቸው፣የተማሪዎችን የቋንቋ ደረጃና ልምዳቸውን ያገናዘበ፣ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቀላሉ እንዲገልጹ የሚያስችል፣በውይይትና

በቡድን ለመጻፍ ምቹ የሆነ፣ግልጽ መመሪያዎች ያሉትና ተማሪዎች እንዲያቅዱ፣እንዲያረቁና እንዲከልሱ የሚያበረታታ እንዲሆን ያስፈልጋል።

- ስለሚጽፉት ነገር ከመነገሩ በፊት ተማሪዎችን ማነሳሳት ያስፈልጋል።
- ተማሪዎች በግል ወይም በቡድን ለማሰራት ከተፈለገ አስቀድሞ ሊነገር ይገባል።
- በቁጥጥር ወቅት ጠቃሚና ገንቢ ምገቤ ምላሽ መስጠት፤
- ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እንዲጻጻፉ፣የጻፉትንም ጽሑፍ ተቀያይረው እንዲያነቡና አስተያየት እንዲሰጣጡ ማበረታታት የሚሉት ይገኙበታል (Attkins 1996፣11)።

2.1.10.5 የጽሕፈት ክሂል አቀራረብ ዘዴዎች

በጽሕፈት ክሂል የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚቻል Raimes (1983፣5-10)፣ Richrds (1990፣106)፣ Byrne (1992፣21) እና Nunan (1989፣36)፡- ውጤት ላይ ያተኮረ አቀራረብ፣ ሂደታዊ አቀራረብ እና ውጤት-ወሂደት አቀራረብ በማለት ገልጸዋል።

1. ውጤት ላይ ያተኮረ የመጻፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴ (Product Focused Approach)

ይህ ዘዴ ከጽሑፍ ክሂል አቀራረብ ዘዴዎች የመጀመሪያው ሲሆን የሚያተኩረውም ተማሪዎች በጻፉት የመጨረሻ ስራ ላይ ነው።ዓላማው ተማሪዎች በሚያከናውኗቸው የጽሕፈት ትምህርት ተግባራት ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙ ማድረግ ነው።በመሆኑም የጻፏቸው ነገሮች ከሰዋስው፣ከዐረፍተ ነገር አወቃቀር፣ከሀሳብ ቅንጅት፣ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ከግልጽነት፣ወዘተ. አኳያ ይገመገማሉ።

በሌላ በኩል Richards (1990፣106) በውጤት ላይ ያተኮረ የጽሕፈት ክሂል አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች በተለያዩ አንቀጾችና ጸሑፎች የማዋቀር ቅንብር ስልት ላይ ልምምድ እንዲያደርጉ ይመራቸዋል ይላሉ።ምክንያቱን ሲገልጹ የዘዴው ትኩረት ተማሪዎች ስህተት የሌለበት ጽሑፍ እንዲጽፉ ማስቻል ስለሆነ የተፈለገውን የጽሑፍ ቅርጽ እንዲያጠኑ በማድረግ ወደ ፊት ታዘው በሚጽፉት ነገር ላይ ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙ ያደርጋቸዋል ይላሉ።እንዲሁም አተገባበሩን ተማሪዎች ሞዴል ዐረፍተ ነገርን ደግመው እንዲጽፉ የሚጋብዝ መልመጃ በመስጠት፣ክፍ ወዳለው አንቀጽ ወደ መጻፍ የሚያሸጋግር መልመጃ በመስጠት፣አንዳንድ ጊዜም ከአንድ ዐረፍተ ነገር ቅርጽ ወደ ሌላ ዓይነት ዐረፍተ ነገር ቅርጽ የመቀየር ተግባራት ለማከናወን የሚጋብዝ መልመጃ በመስጠት የሚተገበር መሆኑን ያብራራሉ።ዋናው ትኩረቱ በሰዋስው፣ በቅርጽና በሥርዓተ ነጥብ ከመሆኑም ባሻገር ተማሪዎችን ስሕተት የመፍጠር አጋጣሚ እንዲያገኙ ጥርት በማድረግ ልዩ ሥፍራ ይሰጣል።

ውጤት ላይ ባተኮረ የጽሕፈት ትምህርት አቀራረብ ውስጥ የሚገኙ ተግባራት፡- ውስን ጽሕፈት (Controlled writing) ፣መር ጽሕፈት (Guided writing) እና ነጻ ጽሕፈት (Free writing) በመባል በሦስት ይከፈላሉ (Richards 1990፣107)። ስለዝህ የጽሕፈት ተግባራት ሲገልጹ በውጤት ላይ ያተኮረ የጽሕፈት ክሂል አቀራረብ ዘዴ መልመጃዎች ሁል ጊዜ የሚጀመሩት በውስን ጽሕፈት መልመጃ ነው።ከዚያም ቀስ በቀስ ወደ ነጻ የመጻፍ ክሂል መልመጃ ያመራሉ በማለት ገልጸዋል፤

ሀ. ውስን-ጽሕፈት (Controlled writing)

የውስን ጽሕፈት መልመጃ በአብዛኛው በጀማሪ ተማሪዎች ለሚካሄድ የጽሕፈት ትምህርት የሚቀርብና ተማሪዎች ወደ መር ጽሕፈት ከመሸጋገራቸው በፊት የሚለማመዱበት የመጀመሪያው መልመጃ ነው።በውስን ጽሕፈት ደረጃ ተማሪዎች

ስራቸውን የሚሰሩት የተሰጣቸውን ትዕዛዝ በአግባቡ በመከተል ነው።የክንውኑ ዓላማም ከስህተት የጸዳ ዓረፍተ ነገርን ወይም አነስተኛ ጽሑፍን እንዲጽፉ ለተማሪዎች ዕድል መስጠት ነው።በውጤት ላይ ያተኮረ አቀራረብ ውስን የጽሕፈት መልመጃ ዓላማው ስህተትን በማስወገድ ላይ መሆኑንና ለመማር-ማስተማር የሚቀርቡት መልመጃዎችም ማሰብንና ፈጠራን የማይጠይቁ ናቸው ብሎ መናገር ይቻላል (McDonough and Shaw 1993፣178 እና Harmer 1991፣109)። በክፍል ውስጥ የሚከናወኑት ተግባራትም፤

- ባዶ ቦታዎችን መሙላት፤
- ሞዴል ዐረፍተ ነገር አስመስለው እንዲጽፉ ማለማማድ፤
- ዐረፍተ ነገሮችን ማያያዝ፤
- በሰንጠረዥ የቀረቡ ቃላትን በማቀናጀት አረፍተ ነገር መስራት፤
- ቅደም ተከተላቸው የተዘባ ቃላትን በማስተካከል ዓረፍተ ነገር መገንባት፤
- ዓረፍተ ነገሮችን ማያያዝና ሌሎችም ይገኙባቸዋል (Raimes 1983፣11)።

ለ. መር-ጽሕፈት (Guided writing)

ይህ የጽሕፈት ደረጃ ተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ወደ ነጻ የጽሕፈት መልመጃ የሚያሸጋግር ድልድይ ነው።እንደ Pincas (1982፣126) አገላለጽ በመር የጸሕፈት መልመጃ ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ የመጨመር ዕድል ይኖራቸዋል።በመሆኑም ከውስን የጽህፈት መልመጃ ይልቅ በዚህ ደረጃም ተማሪዎች የተሻለ ነጻነት አላቸው፤ነጻነቱ ግን በነጻ ጽሕፈት ጊዜ ከሚያገኙት ያነሰ ነው።ምክንያቱም በመር የጽሕፈት መልመጃ ጊዜ ተማሪዎች ሊከተሉት የሚገባ ሞዴል ይሰጣቸዋል በማለት ያስረዳሉ።

በሌላ መልኩ Raimes (1983፣103) መር የጽሕፈት መልመጃ ቁጥጥር ከውስን ጽሕፈት ያነሰ የሚሆነው የሚሰጣቸው ጽሑፍ ቅርጽና ይዘት ሙሉ በሙሉ ለተማሪዎች ስለማይቀርብላቸው ነው ይላሉ።ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለውም በመር ጽሕፈት ጊዜ ተማሪዎች አንድ የተጀመረውን ውጥን ታሪክ፣ደብዳቤ፣አንቀጽ፣ ወዘተ. እንዲያሟሉ የሚታዘዙ መሆኑን ነው።የሚጨምሩት ሀሳብ ግን በጅምር ከቀረበው የአንቀጽ ሀሳብ ጋር የሚስማማ መሆን ይኖርበታል።እነዚህ የጽሕፈት ተግባራት ለተማሪዎቹ መነሻ የሚሆን ፍንጭ በመስጠት የራሳቸውን ሀሳብ አክለው በጽሑፍ እንዲያቀርቡ የሚያለማምድ ነው (Raimes (1983፣103)።የሚቀርቡት ተግባራትም፤

- በሰንጠረዥ የቀረቡ ሀሳቦችን ወደ ጽሁፍ መቀየር፣
- በጅምር የቀሩ ጽሑፎችን(ውጥን ታሪኮችን፣ደብዳቤዎችን፣ቅጾችን፣ወዘተ.) መጨረስ፣
- የተዘጋጀ ቢጋር ተጠቅሞ አንቀጽ መጻፍ፣
- የቀረቡትን ነገሮች በማወዳደርና በማነጻጸር በጽሑፍ መግለጽ እና
- ተከታታይ ጥያቄዎችን በማቅረብ ለጥያቄዎቹ የቀረቡትን ምላሾች መነሻ አድርጎ አጭር ታሪክ መጻፍ የሚሉት ይገኙባቸዋል (Attkins 1996፣11)።

ሐ. ነጻ-ጽሕፈት (Free writing)

ነጻ ጽሕፈት መልመጃ ከመር የጽሕፈት መልመጃ ቀጥሎ የሚመጣ በውጤት ላይ ያተኮረ የአቀራረብ ዘዴ የመጨረሻ ደረጃ ነው።ይህ የጽሕፈት መልመጃ ከመርም ይሁን ከውስን መልመጃዎች የበለጠ ለተማሪዎች ሰፊ ነጻነትን ይሰጣል። Pincas (1982፣106) እንደሚገልጹት፣ ነጻ የጽሕፈት መልመጃ ለተማሪዎች በሚሰጣቸው ርዕስ ወይም በመረጡት ሀሳብ በራሳቸው የሚያከናውኑት መልመጃ ነው። ተማሪዎች ጽሑፉን የሚጽፉት ከራሳቸው አፍልቀው ሲሆን በሚጽፉት ነገር ላይም የሚደረገው

ቁጥጥር የላላ ነው።ከዚህ በተጨማሪም የነጻ ጽሕፈት መልመጃ ትኩረት የሚሰጠው ሁሉንም ነገር እንዲጽፉ ሳይሆን የተማሩትን ለመጻፍ ብቻ ነው።ተማሪዎች በውስንና በመር የጽሕፈት መልመጃ ያገኙትን ዕውቀትና ልምድ በማቀናጀት ራሳቸውን ችላ ብለው መጻፍ ይኖርባቸዋል።በነጻ የጽሕፈት ትምህርት መልመጃ ምንም እንኳ ተማሪዎች በውስንና በመር የጽሕፈት መልመጃዎች የተማሩትን እንዲከተሉ ቢደረግም ሀሳቡን የሚያቀናጁት በራሳቸው ስለሆነ ሰፊ ነጻነት አላቸው። እንደ Raimes (1983፣7) ገለጻ ደግሞ ነጻ ጽሕፈት ለሰዋስዋዊ አጠቃቀምና ለስርዓተ አጻጻፍ እንዲሁም ለትክለኛነት ትኩረት የሚሰጥ ቢሆንም ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ የመግለጽ ዕድል አላቸው።

- **በውጤት-ተኮረ የጽሕፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ላይ የተሰነዘሩ ትችቶች**

Richards (1990፣112) Murry (1980)ን ጠቅሰው ይህ ዘዴ የተማሪዎች የመጨረሻ የጽሕፈት ስራ ውጤት እንጂ የአጻጻፋቸውን ሂደት እንደማያሳይ ይገልጻሉ። በአሁኑ ጊዜ ስለ ጽሕፈት ትምህርት የሚያጠኑ ምሁራንም በውጤት ላይ ያተኮረ የጽሕፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ጽሕፈትን ለማስተማር ችግሮች አንዳሉበት ያመለክታሉ።ምክንያቱንም ሲገልጹ ዘዴው የሚያተኩረው አንድ የጽሕፈት ተግባር "እንዴት ሆኖ ተጠናቋል?" የሚለውን እንጂ አንድን ጽሑፍ ለመጻፍ "ምን ዓይነት አሳሄድ እንከተል?" የሚለውን አያመለክትም በማለት ያብራራሉ።በተጨማሪም ይህ ዘዴ በተጻፈው ነገር ትክክለኛነት ላይ ልዩ ግምት አለው።በዚህ የአቀራረብ ዘዴ ተማሪው የሚያውቀው ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር እንዴት ማዋቀር እንደሚችልና የተለያዩ የጽሑፍ ቅርጾችን እንዴት ማደራጀት እንዳለበት ነው።ይሁን እንጂ ይህ ውጤት ላይ ያተኮረ የጽህፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተማሪው በራሱ መንገድ ሓሳብ አፍልቆና አደራጅቶ የራሱን ጽሑፍ እንዴት መጻፍ እንደሚችል አይገልጽም በማለት ይተቻሉ።

በውጤት ላይ ያተኮረ የጽሕፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴን አስመልክተው Pincas (1982፣24) እንደሚገልጹት በዚህ ዘዴ ተማሪው የሚያከናውነው በመምህሩ አድርግ ተብሎ የታዘዘውን ብቻ በመሆኑ የፈጣሪነት ባህርይው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው።

በሌላ በኩል Raimes (1983፣17) በውጤት ላይ ያተኮረ የጽሕፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች እንዴትና ለምን እንደሚጽፉ ከማሳየት ይልቅ የጽሑፍ ቅርጾችንና የሰዋስው ህጎችን ተከትለው እንዲጽፉ የሚገፋፋ ነው።በውጤት ላይ ያተኮረ አቀራረብ ለሂደታዊ ክሂሎች ዋጋ አይሰጥም።የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋና ትኩረትም ጽሑፉ በሚዘጋጅበት ሂደት ላይ ሳይሆን ተጠናቆ በሚቀርበው ስራ ላይ ከመሆኑም ባሻገር ውጤቱም የሚለካው ከትክክለኛነት አንጻር ነው (Badger እና Goodith 2000)።

2. ሂደታዊ አቀራረብ (Process Approach)

ሂደታዊ የጽሕፈት ትምህር አቀራረብን በተመለከተ Raimes (1983፣10) ላይ በአሁኑ ጊዜ የጽሕፈት ትምህርት በውጤት ላይ ካተኮረ አቀራረብ ይልቅ ወደ ሂደት-ተኮር የመለወጥ አዝማሚያ እያሳየ መጥቷል።በሂደት ተኮር ተማሪዎች የሚጽፉበትን ተግባርና ተደራሲያንን ከማሰብ አልፈው "እንዴት አድርጌ እጽፋዋለሁ? እንዴትስ አድርጌ እጀምረዋለሁ?" የሚሉትን ጥያቄዎች ማሳብ ይኖርባቸዋል።የዚህ አቀራረብ ትኩረት በመጻፍ በተደረሰበት ውጤት ላይ ሳይሆን ተማሪዎች ለመጻፍ በሚያልፉባቸው ሂደቶች ላይ ነው።

ሂደታዊ የጽሕፈት ትምህርት አቀራብ ዘዴ የሚያተኩረው ተማሪው አንድን የጽሕፈት ተግባር እንዴት አድርጎ ጀምሮ ከዚያም እንዴት አድርጎ አቀናጅቶ በራሱ መጻፍ ይችላል በሚለው ላይ ነው።በመሆኑም ይህ የአቀራረብ ዘዴ ተማሪ-መራሽ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ትልቁን ሚና የሚጫወተው ተማሪ ነውና።

Richards (1990፣111) በሂደታዊ አቀራብ የመምህሩ ሚና በክፍል ውስጥ ያለውን የመማር-ማስተማር ሂደት ማመቻቸት ነው።መምህራን ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ እየተንቀሳቀሱ በማየት ተማሪዎችን ያበረታታሉ፤የሐሳብና የምክር እርዳታ ያደርጋሉ፤የሚያስፈልጉ ነገሮች ካሉም ያሟላሉ። በሂደታዊ የጽሕፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ መማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ አንድ የተሟላ ሀሳብ የሚያስተላልፍ ጽሁፍ ለመጻፍ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸው የተለያዩ የተግባር ደረጃዎች እንዳሉ Hedge (1988፣15) እና Richards (1990፣118) ይገልጻሉ።እነዚህ ምሁራን የጠቀሷቸው የተለያዩ ደረጃዎች በሂደታዊ አቀራረብ የጽሕፈት ትምህርት ተግባራትን በሂደት ለማሳየት የቀረቡ ሲሆኑ ይዘውት የተነሱት መሰረታዊ ሓሳብም ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነው።ከዚህ ቀጥሎ Richards (1990፣108) በሶስት ደረጃ ከፍለው ያስቀመጧቸው የዘዴው የአቀራረብ ስልቶች በቅደም ተከተል ቀርበዋል።

ሀ. ቅድመ ጽሕፈት (Pre-Writing)

ይህ ደረጃ በሂደት-ተኮር ውስጥ ካሉት የጽሕፈት ትምህርት አተገባበር የመጀመሪያው ነው። ቅድመ ጽሕፈት ሊያካትታቸው ከሚገቡ ነገሮች መካከል የሚጽፉበትን ርዕስ መምረጥ፣ስለ ርዕሱ ማሰብ፣ ተደራሲያንን መመልከትና ለምን ዓላማና ተግባር እንደሚጽፉ ማወቅ ይገኙባቸዋል (Richards 1990፣109)። ተማሪው መረጃ ለመሰብሰብ፣አንባቢውን ለመገመት፣ ዓላማውን ለመወሰንና የመጀመሪያ ንድፉን ለማቀድ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ያጠቃልላል።

ቅድመ ጽሕፈት ለመጻፍ የሚያስችል ሀሳብ የሚሰበሰብበት ጊዜ ነው።አንድ ጽሑፍ ከመጻፉ በፊት ስለሚጻፍበት ርዕሰ ጉዳይ ይታሰባል፤ርዕሱ ምን ዓይነት ስፋትና ጥልቀት አለው? ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሀሳቦችስ ማግኘት የሚቻለው እንዴት ነው? እና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ የሚፈለግበትና የአእምሮ ዝግጅት የሚፈተሽበት ጊዜ ነው።ይህ ደረጃ ድንገት በአእምሮ የሚመጣ ማንኛውም ሀሳብ

የሚሰበሰብበት ወቅት ነው።እነዚህን የተለያዩ መረጃዎች ለመሰብሰብ ከሚያስችሉ ነገሮች መካከል አራቱ የቋንቋ ክሂሎች ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው።

ለ. የጽሕፈት ጊዜ (While writing)

ይህ ከሂደታዊ የጽሕፈት ትምህርት አተገባበር ዘዴዎች መካከል ሁለተኛው ደረጃ ነው።የጽሕፈት ጊዜ ሀሳብን በወረቀት ላይ በረቂቅ መልክ ማሰፈርን ይመለከታል። ደረጃውም ትክክለኛ የጽሕፈት ተግባር የሚጀመርበት ሲሆን ተማሪው በቅድመ-ጽሕፈት ደረጃ የሰበሰባቸውን ሃሳቦች በረቂቅ መልክ ወረቀት ላይ የሚያሰፍርበት ጊዜ ነው።ተማሪው በተጨማሪም ሀሳቦቹን አብራርቶ ግልጽ በሆነና አሻሚነት በሌለው ቋንቋ የሚጻፍበት፣ለጽሑፉ ቅርጽ በራሱ የሚፈጥርበት ደረጃ ነው (Richards 1990፣109)።

እንደ Hedge (1988፣11) ገለጻ፣ደግሞ በዚህ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት በርካታ ናቸው።ለአብነት ያህል ማቀድ - ማርቀቅ - መከለስ - ደግሞ ማቀድ ይጠቀሳሉ። በመከለስ ደረጃም ከሚካሄዱት ክንውኖች ቀድሚያ የሚሰጠው የይዘት ትክክለኛት ነው።ተማሪዎች የተጻፈውን መገምገምና የሚጨመሩ ወይም የሚቀነሱ ሀሳቦች ካሉ ማስተካከል ይኖርባቸዋል።ስለዚህ በመማር-መስተማር ሂደት ተማሪዎች የመጀመሪያውን ረቂቅ ሲጽፉ መግለጽ በፈለጉት ይዘት ላይ ማተኮር አለባቸው።

ሐ. ድኅረ ጽሕፈት (Post writing)

ይህ ደረጀ ከሂደታዊ የጽሕፈት ትምህርት አተገባበር መካከል የመጨረሻው ነው። ድኅረ ጽሕፈት ወይም ማቃናት የተጻፈው ነገር የሚገመገምበትና በጽሑፍ አማካይነት ለማስተላለፍ የተፈለገው ነገር በትክክል እንዲተላለፍ የመጨረሻ ማስተካከያ የሚደረግበት ነው።ተማሪው መልእክቱን፣ቅርጹንና አንባቢውን የሚያጤንበት፣ግልጽነቱን የሚገመግምበትና ጽሑፉን ደግሞ በማንበብ ለአንባቢው

በሚመች መልኩ መቅረቡን የሚያረጋግጥበት የክንውን ደረጃ ነው (Richards 1990፣109)።

ድኅረ ጽሕፈትን አስመልክቶ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ድኅረ ጽሕፈት በቅድመ እና በጽሕፈት ጊዜ የተሰበሰቡትና የተረቀቁት ሀሳቦች ተገቢነት የሚገመገምበት ደረጃ ነው።በአጠቃላይ ተማሪው ያረቀቃቸውን ሀሳቦች ከዓላማውና ከአንባቢው አኳያ ሊተላልፍ የተፈለገው መልእክት በትክክል መቅረብ ያለመቅረቡን የሚመረምርበት ነው።

- **በሂደታዊ የጽሕፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ላይ የተሰነዘሩ አስተያቶች**

እነ Attkins (1996፣120) ዘዴውን አስመልክተው "ሂደታዊ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ድክመት ሙሉ በሙሉ ነጻ ጽሕፈትን ተጠቅሞ ተግባራዊ ማድረግ የተማሪዎችን የጽሑፍ ችሎታ ያዳብራል ብሎ መገመቱ ነው" ይላሉ።

Horowitz (1986፣445) በበኩላቸው ሂደታዊ የጽሕፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በመማር- ማስተማሩ ሂደት የሚከተላቸው የማስተማሪያ ስልቶች አሉታዊ ተጽእኖ ያላቸው መሆኑን ያስረዳሉ።ይህም በአጻጻፍ ሂደቱ ተማሪዎች ብዙ ረቂቆችን እንዲጽፉ የሚሰጠው ትኩረት ሁል ጊዜ ለሚጽፉት ድርሰት ብቁ አያደርጋቸውም። ለቢጤ እርማት ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱም ተማሪዎች ስለራሳቸው ችሎታ ያላቸው ግምት የተሳሳተ እንዲሆን ያደርጋቸዋል በማለት ይተቻሉ።

3. ውጤት-ወሂደት አቀራረብ (Process-Product Approach)

ይህ የጽሕፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በስፋት አገልግሎት ላይ የዋሉትን በውጤት ላይ ያተኮሩና ሂደታዊ የጽህፈት ትምህርት አቀራረቦችን በማጣመር የቀረበ ዘዴ ነው።እነዚህ ዘዴዎች በተናጠል ውጤታማ ባለመሆናቸው ክፍተታቸውን ለመሙላት የቀረበ ነው።የጽሕፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ለውጤትም ሆነ ለሂደት እኩል ትኩረት መሰጠት እንዳለበት ያምናል።የተማሪውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የጽሕፈት ትምህርት ይዘቶችን ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን ይጠቁማል።በተጨማሪም የተማሪዎች ጽሕፈት ልምምድ የተወሰነ ዓላማ እና ግብ ሊኖረው ይገባል የሚል የአሰራር መርህ ያለው ነው (Dyer (1996፣312)።

Horowitz (1986፣447) እንደገለጹት ሁለቱን አጣምሮ በስራ ላይ ያዋለው ውጤት-ወሂደት ዘዴ በኋላ ተግባር-ተኮር (Task-based) ተብሎ እንደዳበረም ይገልጻሉ።አያይዘውም ይህ ዘዴ አንባቢን መሰረት አድርጎ በተለይ ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ተማሪዎች ውጤታማ የጽሕፈት ማስተማሪያ ሆኖ እንደተገኘ ያስረዳሉ።

እንደ Raimes (1983፣11) ገለጻ በአጠቃላይ የጽሕፈት ትምርት አቀራረብ ዘዴዎች በተናጠል የሚተገበሩ አይደሉም።በክፍል ውስጥ በአንድ ዘዴ ላይ ብቻ ተመስርቶ (ሌሎች ዘዴዎችን ሳያካትት) ጽሕፈትን ማስተማር አስቸጋሪ ነው።ለምሳሌ በሂደታዊ አቀራረብ ዘዴ ተጠቅሞ በክፍል ውስጥ የሚያስተምር መምህር ከተማሪዎች አቅምና ፍላጎት አንጻር እንደ አስፈላጊነቱ ከሌሎች ዘዴዎች የውጡትን የማስተማሪያ ስልቶች መጠቀም አለበት።ሞዴል አንቀጾች፣ውስን ጽሕፈት፣ነጻ ጽሕፈት፣የዓረፍተ ነገር መልመጃዎችና የአንቀጽ ትንተና የአቀራረብ ዘዴዎች ጠቃሚዎች ናቸው።የጽሕፈት ትምህርት አቀራረብ አንድን ዘዴ ብቻ መሰረት ያደረገ ሳይሆን ከሁሉም ዘዴዎች የተውጣጣ መሆን ይኖርበታል።

በአጠቃላይ ከላይ ከተገለጹት የምሁራን ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው አንድን ዘዴ ብቻ ተጠቅሞ ማስተማር እንደማይቻልና የጽሕፈት ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች የተለያየ የማስተማሪያ ስልቶች ቢኖሯቸውም በክፍል ውስጥ ባላቸው አተገባበር የተደጋገፉነት ባህርይ ስላላቸው በስብጥር እንደሚቀርቡ ነው።

2.2 ቀደምት ጥናታዊ ጽሑፎች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥ የሆኑ ስራዎችን በተመለከተ በአማርኛ ቋንቋ ማስረሻ አላዜ (2001)፣በእንግሊዝኛ ደግሞ ሳራ አቦጋይ (1989) የሚገኙ ሲሆን ሌሎቹ ግን በፍተሻ ላይ ብቻ ያተኮሩ ናቸው።

ማስረሻ አላዜ 2001ዓ/ም "በመርዓዊ ከተማ በአጸደ ህጻናትና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (1-4) የሚገኙ መምህራን የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው የጨዋታ ዓይነቶችና ክንውኖች" በሚል ርዕስ የተሰራ ሲሆን ዓላማው፡-በትምህርታዊ ጨዋታዎች ቋንቋን ማስተማር ለተማሪዎች ትምህርት ውጤታማነት ያለውን ሚና መመርመር ነው።ውጤቱም በትምህርታዊ ጨዋታዎች አማካይነት ቋንቋን ማስተማር ለተማሪዎች ትምህርት ውጤታማነት አዎንታዊ አስተዋጽኦ መኖሩን ጠቁሟል።

የማስረሻ አላዜንና ይህን ጥናት የሚያመሳስላቸው ሁለቱም በአማርኛ ቋንቋ በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ላይ ሙከራዊ ጥናት ማድረጋቸው ሲሆን የሚለያዩአቸው የሚከተሉት ነጥቦች ናቸው።

የማስረሻ አላዜ ጥናት የተካሄደበት ቦታ መርዓዊ ከተማ፣ ጥናቱ የተተኮረበት የክፍል ደረጃ፡-አንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ከ1-4፣ ዘዴው ተማሪ ተኮር ሆኖ በትምህርታዊ ጨዋታዎች የአማርኛ ቋንቋን ማስተማር፣ ትኩረት የተደረገባቸው የቋንቋ ይዘቶች ቃላት፣ንግግርና ጽህፈት ሲሆኑ ይህ ጥናት ግን በሙዱላ ከተማ፣ በሁለተኛ ደረጃ ዘጠነኛ ክፍል፣ በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ፡- በጽሕፈት ክሂል ሙከራዊ ጥናት በማድረጉ ሁለቱም የተለያዩ ጥናቶች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

ሳራ አቦጋይ(1989) "English language teaching games and activities in Ethiopia primary schools" በሚል ርዕስ በትምህርታዊ ጨዋታዎች አዲስ አበባ በሚገኝ አንድ አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤት ጥናት አድርጋለች። በጥናቷ በትምህርታዊ ጨዋታዎች የማዳመጥ ክሂልን ማስተማር ያለውን ሚና ለማሳየት ሞክራለች።

ይህ ጥናት ከሳራ ጥናት የሚለየው የሳራ ጥናት በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በሁለተኛ ደረጃ ዘጠነኛ ክፍል ላይ ያተኮረ በመሆኑ ነው።ሌላው የሳራ ጥናት በትምህርታዊ ጨዋታዎች የማዳመጥ ክሂልን ማስተማር ያለውን ውጤታማነት ለማሳየት ያለመ ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት ግን በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ የጽህፈት ክሂልን ማስተማር በተማሪዎች ትምህርት ውጤታማነት ላይ ያለውን ሚና ማሳየት ነው።

ስዩም (1988) "ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ ለዘጠነኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት" በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናት ሂደታዊ አቀራረብ ዘዴን ተጠቅሞ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጽሕፈትን ማስተማር ክሂሉን ለማዳበር ውጤታማ ሆኖ መገኘቱን መረጋገጣቸውን ገልጸዋል።

ሰይድ (1993) "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መጽሓፍ የቀረቡትን የጽሕፈት ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ግምገማ" በሚል ርዕስ በሰባት የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ጥናታቸውን አካሂደዋል።የደረሱበት ማጠቃለያም ተማሪዎች ጽሕፈትን በተግባር በመለማመድ ሂደት የማስተማሪያ ዘዴ አለመለየቱን በመማር-ማስተማር ሂደቱም የሚቀርቡት ይዘቶችና ክንውኖች ለደረጃው በመርሀ ትምህርቱ ከቀረቡት ዝቅ ያሉ መሆናቸውና የጽሑፍ ተግባቦትን ለመፍጠር የሚያስችሉ አለመሆናቸውን እንዲሁም ተማሪውን ለማጻፍ የሚያበረታታ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ተግባራዊ እንዳልሆነ አመልክተዋል።

የስዩምና የሰይድ ጥናቶች በጽሕፈት ክሂል ላይ መካሄዳቸው ከዚህ ጥናት ጋር ቢያመሳስላቸውም እያንዳንዱ ጥናት ሲታይ፤ የስዩም ጥናት፣ "ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ ለዘጠነኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት" ላይ፣ የሰይድ ጥናት ደግሞ "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መጽሓፍ የቀረቡትን የጽሕፈት ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ግምገማ" ላይ፤ እንዲሁም ይህ ጥናት "በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በቡድን ማስተማር ለተማሪ ውጤታማነት ያለውን አስተዋጽኦ በመከራዊ ጥናት መፈተሽ" ላይ ማተኮሩ ጥናቶቹ እንዲለያዩ አድርጓቸዋል።

49

ምዕራፍ ሦስት

3. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት በተማራ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ማስተማር በተማሪዎች ውጤታማነት ላይ የሚኖረውን አስተዋጽኦ በሙከራዊ ጥናት ይፈትሻል።

ጥናቱ ከታለመው ግብ ላይ ይደርስ ዘንድ ዓይነታዊና አሃዛዊ የምርምር ዘዴዎችን በመጠቀም አቀራረቡም ገለጻዊ ይሆናል። በመሆኑም ጥናቱ በሙከራዊ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ ውጤት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በንጽጽር ያሳያል።

3.1 የናሙና አመራረጥ

3.1.1. የቦታና የትምህርት ቤት ናሙና

ጥናቱ የሚያካልለው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን ጠምባሮ ወረዳ የሙዱላ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በምኞት ናሙና የተመረጠ ሲሆን ምክንያቱ አጥኚው አስቀድሞ የተማረበትና አሁንም ቢሆን እየሰራ ያለበት ትምህርት ቤት በመሆኑ ተገቢው ትብብርና መረጃ የማግኘት ዕድሉ እንደሚሰፋ ስለታመነበት ነው።

3.1.2 የክፍል ናሙና

በትምህርት ቤቱ ካሉት ክፍሎች ውስጥ ዘጠነኛ ክፍል በታላሚ ናሙናነት ተመርጧል።ምክንያቱም ከአስርኛ እስከ አስራ-ሁለተኛ ክፍሎች ያሉት ተማሪዎች በብሔራዊ ፈተና ዝግጅትም ይሁን የሚፈልጉትን የትምህርት ዘርፍ በመምረጥ ላይ ስለሚያተኩሩ ነው።

3.1.3 የምድብ ናሙና

በትምህርት ቤቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የሚማሩባቸው አስር ክፍሎች አሉ።ከነዚህ መካከል ጥናቱ ሙከራዊ እንደመሆኑ መጠን ለሙከራዊና ለጥብቅ ቡድን የሚውሉ ሁለት ክፍሎች በተራ ዕጣ ናሙና ይመረጣሉ።

3.1.4 የሙከራዊ ቡድኑ የክፍል ውስጥ ክንውን ናሙና

የሙከራዊ ቡድኑ ተመሪዎች ለአንድ ወር ከአስራ አምስት ቀናት በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በአጥኚው፣ጥብቅ ቡድኑ ደግሞ በመምህር-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በሌላ መምህር እንዲማሩ ተደርጓል።ለክፍል ደረጃው በሳምንት ሁለት ክፍለ ጊዜ የተመደበለት ሲሆን አጥኚው ለሁለቱም ክፍሎች ተመሳሳይ የጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን አዘጋጅቷል።

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

3.2.1 የቅድመ ችሎታና የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች

አስቀድሞ እንደተገለጸው የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ በሙከራዊ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል የሚታየውን የውጤት ተመሳሳይነትና ልዩነት በመፈተሽ በአማርኛ ቋንቋ የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በቡድን ማስተማር ለሙከራዊ ቡድኑ ተማሪዎች ውጤታማነት ያለውን አስተዋጽኦ ማሳየት እንደመሆኑ መጠን በዋናነት የተማሪዎች የቅድመ ችሎታና የድኅረ ችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ሲሆኑ የጽሑፍ መጠይቆች በተጨማሪነት የሚያገለግሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ናቸው።

በዚህ ጥናት የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና የሚሰጠው በሙከራዊ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ያለውን የውጤት ተመሳሳይነትና ልዩነት ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ ነው።

በዚህ ጥናት የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና የሚሰጠው በመካከራዊ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ያለውን የውጤት ተመሳሳይነትና ልዩነት ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ ነው።

የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ውጤት ተማሪዎች በትምህርቱ ካለፉ በኋላ ለሚያስመዘግቡት ውጤት ማነጻጸሪያ ሆኖ ያገለግላል።

የድኅረ ችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች የተወሰነ ትምህርት ከተማሩ በኋላ የሚቀርብ ፈተና ሲሆን ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ የሚያሳዩትን ብቃት ይመዝናል።

3.2.2 የጽሑፍ መጠይቅ

ተጠኚ ተማሪዎች የቀረበላቸውን የቋንቋ ትምህርትና የማስተማሪያ ዘዴ መውደድ አለመውደዳቸውን ለማረጋገጥ መሞከር አንዱ የዚህ ጥናት ዓላማ ነው።ስለዚህ ይህንን ሁኔታ ለማረጋገጥ መካራዊ ቡድን ለሆነው ምድብ "G" የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ነበር።ይህ መጠይቅ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ለ63 ተማሪዎች ቀርቧል።ይህም የሆነበት ምክንያት በድኅረ ትምህርት ፈተና የተሳተፉት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች 63 በመሆናቸው ነው።መጠይቁ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣የመጠይቁ የመጀመሪያው ክፍል ያታን፣ዕድሜንና የአፍ መፍቻ ቋንቋን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ታስቦ የተዘጋጀ ነው።የመጠይቁ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ አሥራ ሁለት ጥያቄዎችን ያካተተ ነው።የጥያቄዎቹ ይዘትም በጽሕፈት ክሂል ላይ ያተኮረ አዎንታዊ (positive) እና አሉታዊ (Negative) አቀራረብ ያለው ሲሆን፣ ጌትነት 2001፣50 ላይ (Likert rating Scale)ን ጠቅሶ እንደገለጸው ተማሪዎች መልስ በማሰጠበት ወቅት ወደ ገለልተኛ እንዳያደሉ የቀረቡት ምርጫዎችም ወደ አራት ዝቅ እንዲሉ ተደርጓል።

3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ከናሙና ምርጫና ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ቀጥሎ ተገቢ የሆነ የመረጃ ትንተና ለጥናቱ ውጤት እጅግ ወሳኝ ናቸው።በመሆኑም በዚህ ጥናት የሚሰበሰበው መረጃ ውጤት በቅደም ተከተልና በሥርዓት ከተደራጀ በኋላ አሃዛዊና ገለጻዊ በሆነ መልኩ ይተነተናል። በትንተናው በመከራዊ ቡድኑና በጥብቅ ቡድኑ የተመዘገበ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ምዘና ውጤት በንጽጽር ይቀርባል።በመጨረሻም ጥናቱ በሁለቱ ቡድኖች የተገኘውን የፈተና ውጤት በማነጻጸር በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የአማርኛ ቋንቋን ማስተማር ለተማሪዎች ውጤታማነት ያለውን ሚና ይገልጻል።

53

ምዕራፍ አራት

4. የማስተማር ሂደት እና የመረጃ ውጤት ትንተና

4.1 የማስተማር ሂደት

በአማርኛ ቋንቋ የጽሕፈት ክሂልን በተማራ-ተኮር አቀራረብ በቡድን ማስተማር በተማሪ ውጤታማነት ላይ የሚኖረውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ በክፍል ውስጥ ተገኝቶ ማስተማርንና ማለማመድን የሚጠይቅ በመሆኑ ለአንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን (ከመጋቢት 04/2005 ዓ/ም እስከ ሚያዝያ 11/2005 ዓ/ም) የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን አስተምሬአለሁ።

በክፍል ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ትኩረታቸውም፡-መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን ወይም ሐረጋትን በተገቢው ቦታቸው መጠቀም፤ሥርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው በመጠቀም የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት፣የጊዜና የድርጊት ቅደም ተከተል ጠብቆ በአያያገሮችና መሸጋገሪያ ቃላት ወይም ሐረጋት አንቀጽ ጽፎ ማቅረብ፤የተለያዩ የሥራ ደብዳቤ አፃፃፍ ዓይነቶችን ማለማመድ፤ድርሰት ለመሳፍ መከናወን የሚገባቸው ተግባራት መግቢያ፣ሐተታና መደምደሚያ ማሳወቅ እንዲሁም የቅድመ-ጽሕፈት፣ጊዜ-ጽሕፈት እና ድኅረ-ጽሕፈት ተግባራትን በማለማመድ ላይ ነው።

ከዚህ ቀጥሎ ለአንድ ወር ከአስራ አምስት ቀናት በማስተማሩ ሂደት በክፍል ውስጥ የተከናወኑ ሥራዎች፣ለትምህርት ልምምዱ የቀረቡ መልመጃዎችና አጠቃላይ የክፍል ውስጥ መስተጋብሮች በዝርዝር ይቀርባሉ፤

ቀን፡-03/07/2005 ዓ/ም

ሰዓት፡-4፡02

ክፍለ ጊዜ፡-4ኛ

ጥናቱን ለማካሄድ ቀዳሚ ተግባሬ ያደረግኩት ዓላማውን ለትምህርት ቤቱ ማሳወቅና ፈቃድ ማግኘትን ነበር፡፡በዕለቱ የትምህርት ቤቱን ርዕሰ-መምህር ካስፈቀድኩ በኋላ ከክፍሉ መምህር ጋር አገናኝተውኝ ተነጋግረን ስምምነት ላይ እንድንደርስ አደረጉን፤ የክፍሉ መምህርም ወደ መማሪያ ክፍል ይዘውኝ በመሄድ ከተማሪዎቻቸው ጋር ካስተዋወቁኝ በኋላ ለተወሰኑ ወራት እንደማስተምራቸው ገልጸው ክፍሉን ለቀውልኝ ወጡ፡፡

በመቀጠልም ተማሪዎች ስለ ጥናቱ ማወቅ የሚገባቸውን ጉዳይ ማሳወቅና እነሱንም ማነቃቃት ተገቢ ሆኖ ስላገኘሁት አሰፈላጊውን ማብራሪያ እንደሚከተለው ሰጥቻለሁ፡፡

ብዙ ምሁራን እንደሚገልጹት አብዛኞቹ ተማሪዎች ለጸሐፈት ክሂል የሚሰጡት ቦታ ከተቀሩት የቋንቋ ክሂሎች ጋር ሲነፃፀር እጅግ ዝቅተኛ ነው፤ከመባፍ ይልቅ ማዳመጥ፤መናገርና ማንበብ ይፈልጋሉ፡፡ጽሕፈትን የሚፈልጉት ለትምህርታቸውና ለፈተና ብቻ ነው፡፡ነገር ግን የጽሕፈት ክሂል መዳበር ለተማሪው የሚሰጠው ጥቅም ከዚህ የሰፋ ነው፡፡ጥሩ የመባፍ ችሎታ ተማሪዎች ጥሩ የማሰብ ብልሃት እንዲያዳብሩ ያደርጋል፤መላ መምታትን ፤መጠየቅን ፤ ግምት መስጠትን፤መላምትን ማረጋገጥንና የተደረሰበትን ውጤት መገምገምን እንዲማሩ ያደርጋል፡፡አዘውትሮ የሚጽፍ ተማሪ የሚጽፈውን ይዘት እየከለሰ ይመረምራል፤ያደራጃል፡፡

ከቃላት ጋር ስለሚጫወት የተለያዩ ፍቺዎችን ያውቃል፤የአገላለጽ ስልቱን ያዳብራል፤የራሱን ሓሳብ ማደራጀት ይማራል።ከዚህ በተጨማሪ ጽሑፋቸው በሌላው መነበቡ ስለራሳቸው ያላቸውን ግምት ከፍ ያደርገዋል።ለሌላው አስፈላጊ እንደሆኑ አድርገው ይገምታሉ።

ጽሕፈት መማርን ይፈጥራል።ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ ሓሳባቸውን በተሻለ መንገድ ለመግለጽ ይፈልጋሉ።በጽሑፍ የሚያስተላልፉትን መልእክት ደጋግመው ያስባሉ፤ ይመረምራሉ።እግረ መንገዳቸውንም ስለድርጊትና ቃላት ግንኙነት ይማራሉ።

ጽሕፈት ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን ማዳበር ያስችላል።ተማሪዎች በጽሑፍ ሓሳባቸውን በተሻለ መንገድ ለመግለጽ የሚያስችላቸውን ቃላትና የዓረፍተ ነገር መዋቅር ለመምረጥ የሚያደርጉት ልምምድ የንግግር ክሂላቸው እንዲዳብር ያደርጋል።በተጨማሪም የማዳመጥና የማንበብ ክሂላቸውንም ያዳብራል።የክሂሎች የተቀናጀ እድገት በፋንታው የመማርን ሂደት አስቸጋሪ እንዳይሆን ያደርጋል።የፈጠራ ኃይል መስፋትና የችግር መፍታት ልምድም ከጽሕፈት ክሂል ጋር ተያይዘው ይዳብራሉ በማለት በድሉ 1996፤52 (Doff, 1988)ን ጠቅሰው የገለጹትን አብራራሁላቸው።

እነዚህንና መሰል የጽሕፈት ክሂል ጠቀሜታዎችን ካብራራሁ በኋላ ትምህርቱን በሚማሩበት ጊዜ የሚያገኙትን ጠቀሜታና የሚጠበቅባቸውን ተሳትፎ በሚከተለው መልኩ ገለጽኩላቸው፤

- በማስተምራቸው ጊዜ በአያያዥ ቃላት ዓረፍተ ነገር መመሥረትን፣ሥርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው መጠቀምን፣አንቀጽ መጻፍን አስተዋአ ነድፎ

ድርሰት መፃፍን በተደጋጋሚ ስለሚለማመዱ የሚያስጨንቃቸውና የሚያስቸግራቸው ነገር ሊኖር እንደማይችል፤

- ልምምዱ በቡድን በመወያየት በጋራ ስለሚከናወን በአንድ ሰው ላይ ብቻ ጫና ሊኖር እንደማይችል እና አብሬያቸው በመሆን አስፈላጊውን እገዛ እንደማደርግላቸው፤
- በቡድን ውይይት ጊዜ ጫጫታ ሊፈጠር ስለሚችል ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው መለማመድ እንደሚጠበቅባቸው፤
- በክፍሉ ውስጥ ባሉ ተማሪዎች መካከልም የችሎታ መለያየት ሊኖር ስለሚችል እንዲተጋገዙ ጭምር አሳስቤ በተነገራቸው ጉዳይ ዙሪያ ያላቸውን ፈቃደኝነት ብጠይቃቸው ሁላቸውም ፈቃደኝነታቸውን በጭብጨባ አረጋግጠውልኛል።

ከዚህ በመቀጠል ትምህርቱን ማስተማር ከመጀመሬ በፊት በቀጣዩ ቀን በ04/07/2005 ዓ/ም ፈተና ስለሚሰጥ ራሳቸውን አዘጋጅተው እንዲመጡ ስነግራቸው ትንሽ የመፍራትና የመደናገጥ ነገር ይነበብባቸው ነበር።እኔም ፈተናው አስቀድመው እነሱ ከሚያውቁት ነገር በመነሳት ለማስተማር (የሚመጣጠናቸውን ትምህርት ማራኪ በሆነ መልኩ መስጠት የሚያስችለኝን መረጃ ለማግኘት) ያዘጋጀሁት ፈተና እንደሆነም ማብራሪያ ሰጠኋቸሁ።

በዚህን ጊዜ አንድ ተማሪ "የፈተና የመልስ ወረቀት ማዘጋጀት ያስፈልጋል ወይስ በራሱ በጥያቄ ወረቀቱ ላይ ነው የሚሰራው?" ብሎ ለጠየቀው ተማሪ፤አስፈላጊው ሁሉ በእኔ እንደሚሟላ አብራራሁላቸው።

ከሌሎች ሁለት ተማሪዎች የተነሱ ጥያቄዎች ደግሞ ለፈተናው ዝግጅት ስለሚጠናበት ርዕስ እና ፈተናውን ለመፈተን ስለሚፈጀው ጊዜ መጠን ነበር።እኔም አስቀድሞ "ፈተና ይሰጣል" ሲባል ያደረባቸው ጭንቀት የቀነሰ ቢሆንም ጨርሶ

ከሌሎች ሁለት ተማሪዎች የተነሱ ጥያቄዎች ደግሞ ስለፈተናው ዝግጅት ስለሚጠናበት ርዕስ እና ፈተናውን ስመፈተን ስለሚፈጀው ጊዜ መጠን ነበር።እኔም አስቀድሞ "ፈተና ይሰጣል" ሲባል ያደረባቸው ጭንቀት የቀነሰ ቢሆንም ጨርሶ ያልለቀቃቸው መሆኑን እየተነሱ ካነሱት ጥያቄዎች በመረዳት ፈተናው አጠቃላይ እውቀት የሚጠይቅ እዚያው በጥያቄ ወረቀቱ ላይ ከተገለጸው ነገር በመነሳት የሚመልሱት እና በጣም ቀላል እንደሆነ፣የተፈቀደው ሰዓትም 1፡10 ሆኖ እንደአሰፈላጊነቱ ሊጨመር የሚችል መሆኑን እንዲሁም አብራአቸው በመሆን አሰፈሰጊውን ሁሉ እገዛ እንደማደርግላቸው ስነግራቸው ሁላቸውም ስጋታቸውን አስወግደው ደስታቸውን በጭብጨባ አረጋገጡልኝ፤ክፍለ ጊዜውም ተጠናቅቆ በመደወሉ ተሰናብቻቸው ወጣሁ።

ቀን፡-04/07/2005 ዓ/ም

ሰዓት፡-4፡44

ክፍለ ጊዜ፡-5ኛ

የቅድመ ችሎታ ፈተና የምሰጥበት ቀን ነበር፤በትምህርት ቤቱ 11ኛ እና 12ኛ ክፍል ክሚያስተምሩ መምህራን ሁለት ረዳት ፈታኞች በመያዝ ቀደም ብዬ ነበር የተገኘሁት።

አስቀድሞ ክፍሉን ያስተምሩ የነበሩት መምህር ስመፈተን ፈቃደኛ መሆናቸውን ቢገልጹልኝም፤ጥብቅ ቡድኑን ለማስተማር ከመ/ከራዊ ቡድኑ ጋር የሚያመሳስል የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ፍንጭ እንዳያገኙ በመስጋት ለትብብራቸው አመስግኜ በቂ የሰው ኃይል እንዳለኝ ስነግራቸው በተፈለገበት ሰዓት የሚገኙበትን አድራሻ ሰጥተው ተሰናበቱኝ።

ረዳት ፈታኞቹን አንደኛውን ለመከራዊ ቡድኑ፤ሌላኛውን ደግሞ ለጥብቅ ቡድኑ መደብኩኝ።በዕለቱ የተገኙት ተማሪዎች ቁጥር በሁለቱም ቡድኖች 63 መሆኑን ካረጋገጥኩ በኋላ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ጥያቄ ወረቀቶቹ ታድለው ሁለቱም ቡድኖች በተመሳሳይ ሰዓት እንዲጀምሩ አደረግኳቸው።ፈታኝ መምህራኑንም በፈተናው ወቅት በክፍል ውስጥ ያለውን ፀጥታ በጥብቅ እንዲከታተሉ በመንገር እኔም በተወሰኑ ደቂቃዎች ልዩነት በየክፍሉ በመመላስ ስመለከት የሁለቱም ቡድን ተፈታኞች ሐሳባቸውን በሙሉ በፈተና ጥያቄው ላይ አድርገው ይሰሩ ነበር።ፈተናውም በአንድ ክፍለ ጊዜ የማያልቅ መሆኑን በመገንዘብ አስቀድሜ በ6ኛ ክፍለ ጊዜ በሁለቱም ክፍሎች የሚገቡትን የሂሳብና የጂኦግራፊ መምህራን አስፈቅጄ ነበር።ፈተናው በተፈቀደው ሰዓት ካላለቀ ተጫማሪ ደቂቃ እንደሚሰጥ በተነገራቸው መሰረት ተጨማሪ 10 ደቂቃ ተጨመረላቸው።ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላም የጨረሱ ተማሪዎች አንገታቸውን ቀና፤ቀና ሲያደርጉ እና መጨረሳቸውን በምልክት ሲገልጹ የፈተና ጥያቄ ወረቀቱን ከነመልስ ወረቀቱ ጋር አስረክበው መሄድ እንደሚችሉ የተነገራቸውን ተግባራዊ እያደረጉ መውጣት ጀመሩ።ፈተናው ሲጠናቀቅም ሁለቱም ፈታኞች ወረቀቶቹን ቆጥረው አስረከቡኝ፤አመስግኜ ተረከብኳቸው፤አብረን ወደ ምሳ አመራን።

59

ቀን፡-06/07/2005

ሰዓት፡-3፡22

ክፍለ ጊዜ፡-3ኛ

ይህ ቀን የመማር ማስተማሩ ሂደት የመጀመሪያው ቀን ነበር።አነቃቂና አስተማሪ የሆነ ገጠመኝ ከነገርኳቸው በኋላ የዕላቱን ትምህርት ጀመርን፤አስቀድሞ የተማሩትን እንዲያስታውሱ የክፍል መምህራቸው በምን ላይ እንዳቆመ ስጠይቃቸው አንዱ ተማሪ እጁን አንስቶ ስለተውኔት እንዳስተማሩ ነገረኝ።አኔም በተውኔት ውስጥ ስለተማሩት አንዳንድ አንኳር ነጥቦች በመጠየቅ በዛሬው ዕለት ስለ መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላት ወይም ሐረጋት እንደሚማሩ በመንገር ስለርዕሱ የተዘጋጀ ማስታወሻ አጽፌ አስረዳኋቸው።

በመቀጠልም "በቡድን ሆናችሁ አፍራሽ እና ደጋፊ መሸጋገሪያ ቃላት ወይም ሐረጋት የምትሏቸውን በተለያየ ምድብ ዘርዝራቸው።" የሚል የክፍል ሥራ ሰጠኋቸው። በመካከላቸው እየተዟዟርኩ ስመለከትም ተማሪዎቹ እያንዳንዳቸውን መሸጋገሪያ ቃላት ወይም ሐረጋት አንዱ የረሳውን ሌላው እያስታወሰ ይዘረዝሩ ነበር።አንዳንድ የጨረሱ ቡድኖች እንዲታረመረላቸው ሲጠሩኝ ክፍለ ጊዜው በመጠናቀቁ ተደወለ፤በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ የሁሉም ቡድን ሥራ ስለሚታረም አጠናቅቀው እንዲመጡ በመንገር የዕለቱን ትምህርት አበቃሁ።

ቀን፡-11/07/2005 ዓ/ም

ሰዓት፡-9፡02

ክፍለ ጊዜ፡-4ኛ

በዚህ ቀን የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሁሉም ተማሪ መሥራት ያለመስራቱን ካረጋገጥኩ በኋላ ከዚህ ክፍለ ጊዜ በኋላ ባለኝ ትርፍ ሰዓት አርሜ እንደምመልስላቸው በመንገር ወደ ተጨማሪ የክፍል ውስጥ ክንውን አመራን፡፡

በመማሪያ መጽሐፋቸው ውስጥ ለማስተማሪያነት የተዘጋጀውን ቅንጫቢ የዕለቱ መማማሪያ ርዕስ አደረግኩኝ፡፡

ምንባቡ በእያንዳንዱ ተማሪ እጅ ባለው መጽሐፍ ውስጥ ስለሚገኝ በየግላቸው ለማንበብ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡

የተሰጣቸውን ምንባብ ድምፃቸውን ሳያሰሙ ለአሥር ደቂቃ እንዲያነቡ አደረግኳቸው፡፡

ቀጥሎ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙትን መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን (ሐረጋትን) እንዲነግሩኝ ጠይቄ የሰጡትን ምላሽ በጥቁር ሰሌዳው ከፃፍኩላቸው በኋላ በአያያዥ ቃላቱ ወይም ሀረጋቱና ባያያዙት ሓሳብ ላይ እንዲወያዩ አደረግኳቸው፤ ውይይታቸውንም እየተዟዟርኩ ስመለከት የተጧጧፈ ነበር፤

በመቀጠልም የሚከተሉትን ምሳሌዎች ከሰራሁ በኋላ በምሳሌዎቹ መሰረት በእያንዳንዱ አያያዥ ቃላት ዓረፍተ ነገር መሥርተው እንዲመጡ የቤት ሥራ ሰጠኋቸው፤

እና፣ይሁን እንጂ፣ ሆኖም፣ስለዚህ፣ወይም፣ነገር ግን፣ከዚያም።

ምሳሌ፡-ሀ) በሕይወት ውስጥ የኑሮን ውጣ ወረድ መታገልና መሸነፍ ያስፈልጋል።

(መታገልና ማሸነፍ የሚሉት ቃላት በ "እና" ተያይዘዋል)።

ለ) ኃይሌ በብዙ ቦታዎች በሩጫ ስለተወዳደረና ስላሸነፈ ጥንካሬውን አረጋግጧል።(ስለ ተወዳረና ስለ ስለ አሸነፈ የሚሉት ሐረጎች በ "እና" ተያይዘዋል)።

የዕለቱን ትምህርት ካጠናቀቅኩ በኋላ በገባሁላቸው ቃል መሰረት 10፡30 ደብተሮቻቸውን አርሜ ለመመለስ ሰብስቤ ይገፎ ወጣሁ።

ቀን፡-13/07/2005 ዓ/ም

ሰዓት፡-8፡22

ክፍለ ጊዜ፡-3ኛ

ፈረቃው ከሰዓት በኋላ በመሆኑ አንድ አዝናኝና አስተማሪ ገጠመኝ ለመናገር ፈቃደኛ ተማሪ ካለ ብዬ ብጠይቅ የተወሰኑ ተማሪዎች እጃቸውን አነሱ።እኔም ንቃታቸውን አድንቄ ቀድሞ እጁን ላነሳው ተማሪ ዕድሉን ሰጠሁ፤የሰውነት ክፍሎች በሆድ ላይ አድመው ኋላ ግን ጉዳቱ ለሁሉም እንደደረሰና እንዳላዋጣቸው አውቀው ሁላቸውም የየራሱን ድርሻ ለመወጣት መስማማታቸውን ከነገረ በኋላ ለክፍሉ ተማሪዎች ሀገራችንን ከድኅነት ለማውጣት ተረባርበን የየድርሻችን መወጣት እንዳለብን በማሳሰብ በአጭሩ ሲያጠቃልል ተማሪው በሙሉ አጨበጨበለት፤እኔም አድናቆቴን በመግለጽ አመሰገንኩት።

ከዚያም በመቀጠል "የሥርኣተ ነጥብ አጠቃቀም" የሚለውን ርዕስ በማስተዋወቅ ማስታወሻ አጽፌ አስረዳኋቸው።

በመቀጠልም በቡድን በመወያት ሥርዓተ ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው እያሚሉ እንዲለማዱ ተደርጓል።

በመጨረሻም በቡድን ሆነው እየሰሩ እያለ ክፍለ ጊዜው አልቆ ደወል በመደወሉ በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ እያንዳንዱ ቡድን የሰራው የሚታረም መሆኑን በመግለጽ የዕለቱን ትምህርት አጠቃለልኩኝ።

ቀን፡-18/07/2005 ዓ/ም

ሰዓት፡-4:02

ክፍለ ጊዜ፡-4ኛ

በዚህ ቀን በይደር የቆየውን ርዕስ ለተወሰነ ደቂቃ ከተወያዩ በኋላ ሞዴል የሚሆኑ ሶስት ቡድኖች ለክፍሉ ተማሪ እንዲያቀርቡ እና አድማጭ ተማሪዎች ያልገባቸውን ጥያቄ እያነሱ እንዲነጋገሩ ተደርጓል።

በመቀጠል ተማሪዎችን በተለያዩ ገጠመኞች በማነቃቃት አዲስ ርዕስ አስተዋወቅኩኝ። ከዚያም በርዕሱ በአንቀጽ ምንነት ዙሪያ የሚያውቁትን ነገር ስጠይቅ አንዱ ተማሪ እጁን አንስቶ "አንቀጽ ማለት ስለ አንድ ሓሳብ ብቻ የሚገልጽ የድርሰት አካል ነው"ሲል፣ ሌሎች እጃቸውን ያነሱ ተማሪዎችን ተመለከትኳቸው።ከነዚያም ለአንዷ ዕድሉን ስሰጣት አንቀጽ ኃይለቃልንና ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮችን የያዘ የድርሰት አካል እንደሆነ ገለጸች፤ ሁለቱንም ተማሪዎች በትክክል እንደመለሱ በመግለጽ ካበረታታኋቸው በኋላ ስለድርሰት የሚያብራራ ማስታወሻ አጽፌ አስረዳሁ።

ከዚያም የተለያዩ ርዕሶችን በመስጠት አንቀጽ እንዲጽፉ አደረግኳቸው።የአፃፃፍ ሂደቱንም በተመለከተ መጀመሪያ በቡድን ሆነው ርዕስ እንዲመርጡ፣በመቀጠል በርዕሱ ዙሪያ ሓሳብ እያፈለቁ እንዲወያዩ (መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር እንዲጽፉ)፣ ከዚያም ያንን መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር ወይም ኃይለ ቃል የሚያብራሩ ዓረፍተ ነገሮች እንዲጽፉ፣ የዓረፍተ ነገሮቹን የሓሳብ ፍሰት ጠብቀው በማደራጀት አንቀጽ እንዲጽፉ ፍንጭ በመስጠት ነበር።ተማሪዎቹ በተሰጣቸው መርህ መሰረት ተወያይተው ሓሳባቸውን አፍልቀው ከፃፉ በኋላ ሳያደራጁት በመጠናቀቁ ተደወለ። እኔም በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ካቆምንበት እንደምንጀምር በመንገር አጠቃለልኩኝ።

ቀን፡-20/07/2005 ዓ/ም

ሰዓት፡-3፡22

ክፍለ ጊዜ፡-3ኛ

በዚህ ቀን በቀደመው ክፍለ ጊዜ ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ የቆየውን የአንቀጽ አፃፃፍ ሥርዓት ካቆመበት ጀምረው ሓሳባቸውን አደራጅተው እንዲጽፉ 15 ደቂቃ ተሰጣቸው።

በመቀጠልም የሚከተለው መመሪያ ተሰጥቷቸው ወደ ቀጣዩ ልምምድ አመሩ።

በጥንድ በመሆን የፃፉትን አንቀጽ ከተለዋወጡ በኋላ ፡-

1. የጓደኞቻቸውን አንቀጽ ኃይለ ቃልንና መዘርዝር ዓረፍተ ነገሮችን እንዲለዩ፣
2. አንቀጹ የያዛቸው ዓረፍተ ነገሮች የሓሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁና በኃይለ ቃሉ ከሰፈረው ዋና ሓሳብ ያልወጡ መሆናቸውን እንዲያረጋግጡ፣
3. ዓረፍተ ነገሮቹ ሰዋስዋዊ ስሕተት የሌለባቸው መሆናቸውን እንዲመረምሩ።
4. ጓደኞቻቸው ተገቢ ሥርዓተ ነጥብ መጠቀማቸውን እንዲያረጋግጡ፡

5. ስለመረመሩት አንቀጽ ለጓደኞቻቸው አስተያያየት እንዲሰጡ ተደርጓል።

ከዚያም የተወሰኑ ምሳሌ የሆኑ እና አስቀድሞም ዕድል ያላገኙ ቡድኖች ሥራ እንዲቀርብ ተደርጎ አጠቃላይ ውይይት ተካሂዷል።

በማጠቃለያውም አንቀጽ ሲጻፍ የጊዜና የድርጊት ቅደም ተከተል ተጠብቆ፣ አስፈላጊ የሆኑ አያያገናኞችና መሸጋገሪያ ቃላት ወይም ሐረጋት በተገቢው ቦታ ገብተው፤ የኃይለ ቃልና መዘርዝር ዓረፍተ ነገሮች ሐሳብ ተዛምዶ፣ሰዋስዋዊ ሥርዓታቸውም ተጠብቆ እና ሥርዓተ ነጥቦች በተገቢው ሁኔታ ተሟልተው መቅረብ እንዳለባቸው ማብራሪያ በመስጠት የዕለቱ ትምህርት ተጠናቋል።

ቀን፡-25/07/2005 ዓ/ም

ሰዓት፡-9:02

ክፍለ ጊዜ፡-4ኛ

በዚህ ቀን ስለ ሥራ ደብዳቤ አጻጻፍ ሥርዓት በፊት ለመነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎችን እንደሚከተላው አነሳሁላቸው፤

1. የደብዳቤ ጥቅሙ ምንድነው?
2. የደብዳቤ ዓይነቶች ስንት ናቸው?

ለጥያቄዎች አብዛኞቹ የክፍል ተማሪዎች እጆቻቸውን አነሱ፤ቀደም ብለው ካነሱት ውስጥ ለአንድ ሴት እና ለአንድ ወንድ ተማሪዎች ዕድሉን ስሰጣቸው፣ ለመሥሪያ ቤት የሚጻፍ የደብዳቤ ዓይነት መሆኑን ተናገሩ። ከዚያም ተማሪዎቹ የመለሱት ትክክል እንደሆነ በመንገር ጠቅለል ያለ ምላሽ ከሰጠኋቸው በኋላ የሥራ ደብዳቤ ምንነት የሚገልጽ ማስታወሻ አጽፌ አስረዳኋቸው።

ማስታወሻውን ካስረዳኋቸው በኋላ የሥራ ደብዳቤ ሞዴል አቅርቤ ከላይ የተገለጸውን የሥራ ደብዳቤ አፃፃፍ ሥርዓት መስፈርት ማሟላት፣ያለማሟላቱን እንዲፈትሹ ጠየቅኳቸው።

በመጨረሻውም በቀጣዩ ቀን በተረዱት መሰረት አንድ የሥራ ደብዳቤ ጽፈው እንዲመጡ በመንገር የዕለቱን ትምህርት አጠቃለልኩኝ።

ቀን፡-27/07/2005 ዓ/ም

ሰዓት፡-8፡22

ክፍለ ጊዜ፡-3ኛ

በዚህ ቀን የፃፉትን የሥራ ደብዳቤ ተቀያይረው ከተማሩት ትምህርት መስፈርት አንጻር እንዲገመግሙ ከተደረገ በኋላ የተሰጣቸውን አስተያየት ተቀብለው አስተካክለው እንዲጽፉ ከ15 ነጥብ የሚያገ መሆኑን ስነግራቸው ሁሉም ተማሪ በትኩረት ወደ መፃፍ ተግባሩ አመራ።

ሰፋ ያለ ጊዜ ሰጥቼ ረጋ ብለው እንዲጽፉ አደረግኩኝ፤በመካከላቸውም እየተዟዟርኩ የሚቸግራቸውን ነገር ካገዝኳቸው በኋላ ሲጨርሱ የጻፉትን የሥራ ደብዳቤ ሰብስቤ፣ ታርሞ በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ እንደምመልስላቸው ነግሬ የዕለቱን ትምህርት አበቃሁኝ።

66

ቀን፡-02/08/2005 ዓ/ም

ሰዓት፡-4፡02

ክፍለ ጊዜ፡-4ኛ

በዚህ ቀን ስለ አስተዋጽኦ አነዳደፍ ከማስተማሪ በፊት ስለርዕሱ የሚያውቁትን ሐሳብ እንዲናገሩ በማድረግ የተዘጋጀውን ማስታወሻ አጽፌ አስረዳኋቸው።(አባሪ ስምንት)

ከዚያም ስለ አስተዋትኦ አነዳደፍ የተዘጋጀውን ሞዴል አቀረብኩላቸው እና መጨመር ወይም መቀነስ ያለበት ሐሳብ ካለ በቡድን ሆነው እንዲወያዩ አዘዝኳቸው።

ውይይቱን ከጨረሱ በኋላ ተጨማሪ ማላማመጃ የሚሆን የክፍል ውስጥ ክንውን ተሰጣቸው።

አስቀድሞ ስለ መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላት ወይም ሐረጋት፣ስለሥርዓተ ነጥብ እና አንቀጽ አፃፃፍ የተማሩትን መሰረት በማድረግ ከላይ በአስተዋጽኦ መልክ የተብራራውን ሐሳብ በማገናኘት የተሟላ ድርሰት እንዲጽፉ ተደረገ፤ይህም ተማሪዎች ከአስተዋጽኦ መንደፍ ወደ ድረሰት መፃፍ ተግባር እንዲሸጋገሩ ታስቦ እየተከናወነ ያለ ተግባር ነው።

67

ቀን፡-04/08/2005 ዓ/ም

ሰዓት፡-3፡22

ክፍለ ጊዜ፡-3ኛ

በዚህ ቀን በቀደመው ክፍለ ጊዜ በባፉት ድርሰት ላይ የተወሰነ ወይይት ተደርጎ፣ ያልገባቸው ነገር ተጠይቆ፣ ምጋቤ ምላሽ ከተሰጠ በኋላ ነበር የዕለቱ ርዕስ የተጀመረው።

ስለድርሰት አፃፃፍ የሚያውቁትን ሓሳብ ተጠየቀው የየራሳቸውን ምላሽ ከሰጡ በኋላ የተዘጋጀውን የድርሰት አፃፃፍ ሥርዓት የሚገልጽ ማስታወሻ አጽፌ አስረዳኋቸው።

ከዚያም ከላይ የተሰጠውን ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ስለ አካባቢያቸው የሚያስረዳ አንድ አስረጅ ድርሰት እንዲጽፉ ተደረገ።ድርሰቱን በሚጽፉበት ጊዜም የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል ማከናወን እንዳለባቸው ተነገራቸው።

1. እየተወያያችሁ ርዕስ ምረጡ።
2. በርዕሱ ሊካተቱ የሚገባቸውን ነጥቦች በአስተዋጽኦ መልክ ዘርዝሩ።
3. በሓሳብ የሚቀራረቡ ዝርዝሮችን እየለያችሁ ባንድ ላይ መድቡ።
4. ስለ አንቀጽ በተማራችሁት መሰረት፣የድረሰቱን መጀመሪያ ረቂቅ ፃፉ።

የተመረጡትን ርዕሶች መፃፍ

1. የመኖሪያ አካባቢዬ፤
2. አካል ጉዳተኝነትና ሥራ፤
3. የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ጠቀሜታ፤

ቀን፡-09/08/2005 ዓ/ም

ሰዓት፡-9:02

ክፍለ ጊዜ፡-4ኛ

የድርሰት ሥራ መልሶ፣መላልሶ መከለስን ስለሚጠይቅ በዚህ ክፍለ ጊዜም አስቀድመው የፃፉትን እንዲከልሱና አሰተካክለው በድጋሚ እንዲጽፉ ተደርጓል።

1. የፃፋችሁትን የድርሰት ረቂቅ አንብባችሁ የሥርዓተ ነጥቦችና የሰዋስው ግድፈቶችን በማረም እንደገና ጽፋችሁ አቅርቡ።
2. ድርሰታችሁን ከሌላ ቡድን ጋር በመለዋወጥ ከሐሳብ ፍሰት፣ከሥርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም፣ከድርጊትና ጊዜ ቅደም ተከተል አንጻር ገምግማችሁ የቡድናችሁን አስተያየት ስጡ።
3. ከየቡድኑ የተሰጣችሁን አስተያየት ተቀብላችሁ በጥንቃቄ አሰተካክላችሁ በድጋሚ ፃፉ።

በመጨረሻም ድርሰቱ የተፃፈበትን ወረቀት በመሰብሰብ እና በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ከተማሩት ርዕስ ብቻ ፈተና እንደሚሰጣቸው በመንገር የማስተማር ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ የችሎታ መለኪያ ምዘና ተሰጥቷቸዋል። በማጠቃለያውምዩችሎታ ምዘና የወሰዱ የመከራ ቡድን ተማሪዎች በመሉ የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉት ተደርጓል።

4.2 የመረጃ ውጤት ትንትና

በጥናቱ ዘዴ እንደተጠቀሰው በአማርኛ ቋንቋ የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዘዴ በቡድን ማስተማር ለተማሪ ውጤታማነት ያለውን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ አጥኚው ሁለቱም መካከለኛውና ጥበቅ ቡድኖች በተለያየ የማስተማሪያ ዘዴ ከመማራቸው በፊት የቅድመ-ችሎታ ፈተና አዘጋጅቶ ተማሪዎች ያላቸው የጽሕፈት ክሂል ችሎታ እንዲመዘን አድርጓል።

4.2.1 የቅድመ ችሎታ ምዘና ውጤቶች ትንተና

የመካከለኛና የጥበቅ ቡድኑን የጽሕፈት ክሂል ችሎታ ለመመዘን የሚያስችሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፤(አባሪ-አንድ)

ለጥናቱ ተሳትፊ ቡድኖች በተሰጡት የቅድመና የድኅረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል የታየ ጉልህ ልዩነት መኖር ያለመኖሩን ለመፈተሽ ሲባል ፈተናዎችን በትክክል አርሞ ውጤቱን መገምገምና ማነጻጸር ተገቢ በመሆኑ በፈተናው ውስጥ መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን ወይም ሐረጋትን በተገቢ ሥርዓተ ነጥቦች አሟልቶ የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት፣የጊዜና የድርጊት ቅደም ተከተል ጠብቆ አንቀጽም ይሁን ድርሰት መዛፍን አስመልክቶ የሚከተለውን የህሊናዊነት (Subjectivity) ችግር ለመቀነስ ሲባል ሦስት የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸውን አሥራ አንደኛ እና አሥራ ሁለተኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን በአራሚነት እንዲሳተፉ ተደርጓል። አራሚዎቹ ድርሰት-ነክ ፈተናዎችን ስማረም ይችሉ ዘንድም እነ Atkins (1996፣14) እንደገለጹት፣ድርሰት ማረሚያ የነጥብ አሰጣጥ ገርገዘር መግለጫ ተሰጥቷቸዋል(አባሪ-አሥራ ስምንት)።

ተጠኝ ተማሪዎች ክሃያ ነጥብ ያስመዘገቡት ውጤት በሦስት አራሚዎች በየግል ታርሞ ወደ መቶ ከተቀየረ በኋላ ለሦስት ተካፍሎ አማካያቸው በተራ ቁጥር በዝርዝር ተመዝግቧል (አባሪ-ሁለትና ሦስት)።

በመቀጠል በሦስቱ አራሚዎች ሁለቱ ቡድኖች በጽሕፈት ክሂል ምዘና ያስመዘገቡት ቅድመ ትምህርት ምዘና ውጤት አማካይና መደበኛ ልይይት በንጽጽር እንደሚከተለው ተመልክቷል።

ሠንጠረዥ-1ሀ ፡-ሦስት አራሚዎች ለሁለቱም ቡድኖች የሰጡት የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት አማካይና መደበኛ ልይይት

የፈተና ዓይነት	ምድብ	የተማሪዎች ብዛት	ውጤት	አራሚዎች		
				1	2	3
ቅድመ ትምህርት	9G	63	አማካይ	29.5	29.746	29.7
			መደበኛ ልይይት	6.03	5.85	6.03
	9A	63	አማካይ	29.619	29.7	29.46
			መደበኛ ልይይት	5.14	5.17	4.66

በሰንጠረዥ-1ሀ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በሁለቱም ክፍሎች የሚገኙት ተማሪዎች ቁጥር እኩል 63 ሲሆን በጽሕፈት ክሂል የቅድመ ትምህርት ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት ተቀራራቢነት ይታይበታል።የመከራዊ ቡድኑ ተማሪዎች ምዘና በሦስቱ መምህራን ታርሞ የተገኘው አማካይ ውጤት 29.65 ሲሆን፣ የጥብቅ ቡድኑ አማካይ ውጤት ደግሞ 29.6 ነው።በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት 0.05 ነው።በመሆኑም ከልዩነቱ ይልቅ ተቀራራቢነቱ ጎልቶ ታይቷል።

እንዲሁም የመ·ከራዊ ቡድኑ መደበኛ ልይይት በሦስቱ መምህራን፡-በአራሚ አንድ 6.026፣በአራሚ ሁለት 5.85፣በአራሚ ሦስት 6.026 የተመዘገበ ሲሆን የጥብቅ ቡድኑን መደበኛ ልይይት በተመለከተ፡-በአራሚ አንድ 5.14፣ በአራሚ ሁለት 5.17፣በአራሚ፣በሦስት4.66 ውጤት ተመዘግቧል።ይህንን በሦስቱ አራሚዎች የተመዘገበው የሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት እና መደበኛ ልይይት ያለውን ተቀራራቢነት ወይም ልዩነት (የጉልህነት ደረጃ) ለመወሰን የሚያስችለው የቲ-ቴስት ስሌት በመሆኑ በመ·ከራዊ እና በጥብቅ ቡድኑ የጽሕፈት ክሂል የቅድመ ችሎታ የምዘና አማካይ ውጤት መካካል ጉልህ ስታትስቲካዊ ልዩነት መኖር ያለመኖሩን ለማረጋገጥ ቀጥሎ የተ-ቴስት ስሌት ውጤት ቀርቧል።

ሠንጠረዥ-1ለ፡-የሁለቱ ቡድኖች የቅድመ ችሎታ ፈተና ውጤት በቲ-ቴስት ሲሰላ፤

የፈተናው ዓይነት	ምድብ	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የነፃነት ደረጃ	የቲ-ስሌት	የቲ-ሠንጠረዥ	የጉልህነት ደረጃ	ጉልህ ልዩነት
ቅድመ ትምህርት	9G	29.65	5.94	124	0.12	1.96	0.025	የለም
	9A	29.6	4.99					

በሠንጠረዥ-1ለ የቀረበው የቲ-ቴስት ስሌት በመ·ከራዊ እና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ያለው የቅድመ ችሎታ የጽሕፈት ክሂል ምዘና በሦስት መምህራን ታርሞ አማካይ የሆነው ውጤት፣በመላምት ፍተሻ ሂደት ከፍተኛ ሚና ከሚጫወተው ከጉልህነት ደረጃ (Level of significance) አንፃር አጥኚው የስህተት ይሆንታ መጠኑን (Probability of error) ወስኗል፤በዚህም የመላምት ዓይነቱ አቅጣጫ የለሽ በመሆኑ የጉልህነት ደረጃው ባለሁለት ጫፍ ፍተሻ ይሆናል።ስለዚህ የጉልህነት ደረጃው 0.05 ለሁለት ይከፈልና 0.025 ይሆናል።

የሰንጠረዥ ዋጋን በተመለከተም የስሕተት ይሁንታ መጠኑን፣የፍተሻውን ዓይነትና የነፃነት ደረጃውን መሰረት አድርጎ በሠንጠረዡ ላይ የሚገኘው የቲ- ሠንጠረዥ ዋጋ 1.96 ሲሆን አገልግሎቱም ከሚገኙት ዋጋዎች ጋር በማወዳደር የተመቱትን መላምቶች በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ነው።

የነፃነት ደረጃው መሰረት የሚያደርገው የጥናት ተሳታፊዎችን ብዛት ሲሆን ከተሰጡን ውጤቶች መካከል ለማቀያየር የሚኖረንን ነፃነት የሚያሳይ ነው።በምርምሩ ውስጥ የሚሳተፉት የናሙና ቡድኖች ሁለት ስለሆኑ እና ከእያንዳንዳቸው አንድ፣አንድ ቁጥር ስለሚቀነስ የነፃነት ደረጃው (n_1+n_2-2) 63+63 -2= 124 ይሆናል።

የቲ-ቴስት ዋጋን በተመለከተም የቲ-ቴስት ስሌት ሲሰላ፣የመከራዊ ቡድኑ መደበኛ ልይይት (Standard Deviation) በ5.94 በአማካይ ከክፍሉ ተጠኚ ተማሪዎች ውጤት ከፍ ወይም ዝቅ ያለ ውጤት ያስመዘገበ ሲሆን፣የጥብቅ ቡድኑ በ4.99 መደበኛ ልይይት ከክፍሉ ተማሪ ውጤት በአማካይ ከፍ ወይም ዝቅ ይላል።እነዚህ ውጤቶች በቲ-ቴስት ቀመር መሰረት ሲሰሉ፣ የቲ-ቴስት ዋጋ 0.12 ይሆናል።

ይህ ከቲ-ቴስት የተገኘው ዋጋ ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ጋር ሲነፃጸር የቲ-ቴስት ዋጋ ያንሳል፤በመሆኑም በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት መካከል ያለው ልዩነት የጎላ አይደለም ማለት ይቻላል።

በአጠቃላይ የቅድመ-ችሎታ ፈተና ውጤቶች እንደሚያመለክቱት በጽሕፈት ክሂል ሁለቱ ቡድኖች የጎላ ልዩነት (Siginificance difference) የላቸውም።ይልቁንም በሁለቱ ቡድኖች መካከል የውጤት መቀራረብ ሁኔታ ጎልቶ ታይቷል። በስታትስቲካዊ ስሌት (ቲ-ቴስት) ውጤት ማረጋገጥ እንደተቻለው በቅድመ ችሎታ ፈተና ውጤት መከራዊና ጥብቅ ቡድኖች የተወሰነ ልዩነት ቢያሳዩም ከጉልህነት ደረጃ አንጻር ግን የጎላ ልዩነት አልታየባቸውም።ስለዚህ ይህን እንደማመሳከሪያ

በመያዝ የሁለቱ ቡድን ተማሪዎች በችሎታ ፈተና (Post-test) የሚያስመዘግቡትን ውጤት ልዩነት በመፈተሽ ለማነጻጸር ያስችላል።

4.2.2 የድኅረ-ችሎታ ምዘና ውጤቶች ትንተና

አጥኚው ጥናቱን ሲያካሂድ ለሁለቱ መከራዊ እና ጥብቅ ቡድኖች የቅድመ ችሎታ ምዘና (Pre-test) ከሰጠ በኋላ መከራዊ ቡድኑ በተማሪ-ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በአጥኚው፣ጥብቅ ቡድኑ ደግሞ በመምህር-ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በሌላ መምህር በተከታታይ ለአንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን የማስተማሩ ሂደት ተከናውኗል። ከዚያም የችሎታ መለኪያ ምዘና (Post-test) ተሰጥቷል።በቅድመ ችሎታ ምዘና የተማሪዎች የጽሕፈት ክሂል እንደተመዘነው ሁሉ በችሎታ መለኪያ ፈተናም የተማሪዎቹን የጽሕፈት ክሂል ለመመዘን የሚያስችሉ ሃያ ጥያቄዎች ለሁለቱም ቡድኖች ቀርበዋል።ጥያቄዎቹ የጽሕፈት ክሂልን የሚመዝኑ ሲሆን ተማሪዎቹ በተማሩት መሰረት በመጻፍ እንዲመልሱ ተደርጓል(አባሪ አንድ)።

ሃያ ጥያቄዎች በሦስት መምህራን ታርመው፣ ከመቶ ፐርሰንት ተቀይረው በተማሪዎች ተራ ቁጥር መሰረት ሰፍረዋል (አባሪ-አምስትና አራት)። የሁለቱ ቡድኖች ውጤት በስታትስቲካው ስሌት መሰረት ከአማካይ ውጤት አንጻር ተሰልቶ በንጽጽር እንደሚከተለው ተመልክቷል፤

ሠንጠረዥ-2ሀ፡-በሦስቱ አራሚዎች የተመዘገቡት የሁለቱም ቡድኖች የችሎታ ምዘና ውጤት አማካይና መደበኛ ልይይት

የፈተና ዓይነት	ምድብ	ውጤት	አራሚዎች			የሦስቱ አራሚዎች
			1	2	3	አማካይ
ድኅረ ትምህርት	9G	አማካይ	59.698	59.9	59.5	59.698
		መደበኛ ልይይት	7.478	7.74	7.66	7.6
	9A	አማካይ	50.46	50.5	50.4	50.476
		መደበኛ ልይይት	5.97	6.05	5.8	5.9

በሰንጠረዥ፡2ሀ እንደተመለከተው በሦስት አራሚዎች የተመዘገበው የመካራዊ ቡድኑ የጽሕፈት ክሂል ምዘና አማካይ ውጤት 59.698 ሲሆን፣የጥብቅ ቡድኑ ውጤት ደግሞ 50.476 ነው።

ሁለቱ ቡድኖች በቅድመ ችሎታ የጽሕፈት ክሂል ምዘና ባስመዘገቡት አማካይ ውጤት የነበራቸው ልዩነት 0.476 ሲሆን በችሎታ ምዘና ግን መካራዊ ቡድኑ የተሻለ ውጤት በማስመዝገብ ልዩነቱ በአማካይ ወደ 9.2 ከፍ ብሏል።

ከቅድመ ችሎታ ምዘና ውጤት አንፃር ሲታይ በችሎታ መለኪያ ምዘና ውጤት በሁለቱ ቡድኖች መካከል ልዩነቱ የጎላ ነው።ይህ የሚያመለክተው ትምህርቱ በተለያየ የማስተማሪያ ዘዴ ከተሰጠ በኋላ በጽሕፈት ክሂል የመካራዊ ቡድኑ ተማሪዎች ከጥብቅ ቡድኑ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን ነው።

መደበኛ ልይይትን በተመለከተ መካራዊ ቡድኑ በሦስቱ መምህራን፡-በአራሚ አንድ 7.478፣በአራሚ ሁለት 7.74፣ እና በአራሚ ሦስት 7.66 የተመዘገበ ሲሆን በሦስቱም አራሚዎች የተመዘገበው አማካይ መደበኛ ልይይት 7.626 ነው።

የጥብቅ ቡድኑን መደበኛ ልይይት በተመለከተ፡- በአራሚ አንድ 5.97፣በአራሚ ሁለት 6.045፣በአራሚ፣በሦስት 5.797 የተመዘገበ ሲሆን የሦስቱ አራሚዎች አማካይ ውጤት 5.9 ነው።

ይህንን በሦስቱ አራሚዎች የተመዘገበው የሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት እና መደበኛ ልይይት ያለውን ተቀራራቢነት ወይም ልዩነት (የጉልህነት ደረጃ) ለመወሰንና በመከራዊ እና በጥብቅ ቡድኑ የጽሕፈት ክሂል የችሎታ የምዘና አማካይ ውጤት መካካል ጉልህ ስታትስቲካዊ ልዩነት መኖር ያለመኖሩን ለማረጋገጥ ቀጥሎ የቲ-ቴስት ስሌት ውጤት ቀርቧል።

ሠንጠረዥ-2ለ፡-የሁለቱም ቡድኖች የችሎታ ምዘና ውጤት በቲ-ቴስት ሲሰላ፤

የፈተናው ዓይነት	ምድብ	አማካይ	መደበኛ ልይይት	የነፃነት ደረጃ	የቲ-ስሌት	የቲ-ሠንጠረዥ	የጉልህነት ደረጃ	ጉልህ ልዩነት
ድኅረ ትምህርት	9G	59.698	7.628	124	6.21	1.96	0.025	አለው
	9A	50.476	5.939					

በሰንጠረዥ-2ለ የቀረበው የቲ-ቴስት ስሌት በመከራዊ እና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ያለው የጽሕፈት ክሂል የችሎታ የምዘና አማካይ ውጤት ልዩነት 9.22 ሲሆን የጉልህነት ደረጃው ባለሁለት ጫፍ ፍተሻ በመሆኑ 0.05 ለሁለት ይከፈልና 0.025 ይሆናል።

የቲ-ቴስት ዋጋን በተመለከተም የቲ-ቴስት ስሌት ሲሰላ፣የመከራዊ ቡድኑ መደበኛ ልይይት (Standard Deviation) በ7.6 በአማካይ ከክፍሉ ተጠኚ ተማሪዎች ውጤት ከፍ ወይም ዝቅ ያለ ውጤት ያስመዘገበ ሲሆን፣የጥብቅ ቡድኑ በ5.9 መደበኛ ልይይት ከክፍሉ ተማሪ ውጤት በአማካይ ከፍ ወይም ዝቅ ይላል።

የነፃነት ደረጃው መሰረት የሚያደርገው የጥናት ተሳታፊዎችን ብዛት ሲሆን ከተሰጡን ውጤቶች መካከል ለማቀያየር የሚኖረንን ነፃነት የሚያሳይ ነው።በምርምሩ ውስጥ የሚሳተፉት የናሙና ቡድኖች ሁለት ስለሆኑ በቲ-ቴስት ስሌት መሰረት የነፃነት ደረጃው (n1+n2-2) 63+63 -2= 124 ይሆናል።

የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋን በተመለከተም የስሕተት ይሁንታ መጠኑን፣የፍተሻውን ዓይነትና የነፃነት ደረጃውን መሰረት አድርጎ በሰንጠረዡ ላይ የሚገኘው የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ 1.96 ነው።

በሠንጠረዡ የቀረበው የቲ-ቴስት ስሌት ውጤት እንደሚያሳየው የጉልህነት ደረጃ 0.025 መሰረት አድርጎ፣ የቲ-ቴስት ዋጋ 6.21 ሲሆን፣ የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ደግሞ 1.96 ነው። የቲ-ቴስት ዋጋ 6.21፣ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ 1.96 ጋር ሲነፃጸር የቲ-ቴስት ዋጋ በመብለጡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት ታይቷል። በልዩነቱም የመከራዊ ቡድኑ የጽሕፈት ክሂል ውጤት የተሻለ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል።

4.2.3 ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተካተተውን የጽሑፍ መጠይቅ የመጀመሪያ ክፍል በሥሩ ያካተታቸው ጥያቄዎች የተማሪዎችን ዳራ ለማወቅ የቀረቡ ናቸው።መጠይቁን ከሞሉት 63 ተማሪዎች የሚከተለው መረጃ ተመዝግቧል።

ሠንጠረዥ-3ሀ፡- የተማሪዎችን ዳራ የሚያሳዩ መጠይቆች

የተማሪው መጠን	1. ፆታ			2. ዕድሜ			3.የአፍ መፍቻ ቋንቋ		
	ወንድ	ሴት	ድምር	ከ14-18	19-22	ድምር	አማርኛ	ሌላ	ድምር
በቁጥር	39	24	63	42	21	63	7	56	63
በመቶኛ	61.9	38.1	100	66.66	33.3	100	11.11	88.8	100

ካላይ በሠንረገቹ የተገለጸውን መመልከት እንደሚቻለው በክፍሉ ውስጥ 39 (61.9%) ወንድ እና 24 (38.1%) ሴት ተማሪዎች ይገኛሉ።

የተማሪዎቹን ዕድሜ በተመለከተ ከ14-18 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ተማሪዎች ቁጥር 42 (66.6%) ሲሆን፣ከ19-22 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ተማሪዎች ቁጥር ደግሞ 21(33.33%) ነው።የአፍ መፍቻ ቋንቋን በሚመለከት ከክፍሉ 7 (11.11%) ተማሪዎች አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ ሲሆን 56 (88.88%) የሚሆኑት ተማሪዎች አፋቸውን በሌላ ቋንቋ የፈቱ ወይም አማርኛን ኢ-አፍ ፈት ናቸው።

ከዚህ የተማሪዎችን የፆታ፣የዕድሜ እና የአፍ መፍቻ ቋንቋ አጣቃላይ ዳራ ማመላከቻ ሠንጠረዥ መረዳት የሚቻለው አብዛኞቹ ወንድ ተማሪዎች መሆናቸውን፣ከዕድሜ አንፃርም በቁጥር በዛ ያሉ ተማሪዎች ከ14-18 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች መሆናቸውንና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎችም በርካታ መሆናቸውን ነው።ስለሆነም የትምህርት ይዘቱ ይህንን የተማሪዎች አቃላይ ዳራ ባገናዘበ መልኩ መቅረብ እንዳለበት ያመላክታል።

ሠንጠረዥ-3ለ፡-የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በቡድን ማስተማር ለተማሪ ውጤታማነት ያለውን አስተዋጽኦ በሚመለከት ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ

	የጽሑፍ መጠይቆች	የስምምነት ምርጫዎች		ያለመስማማት ምርጫዎች (%)		የሚጠበቀው አሉታዊ/ አዎንታዊ መልስ(-)(+)
		ሀ(%)	ለ (%)	ሐ (%)	መ (%)	
1	ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በመሆን የክፍልም ሆነ የቤት ሥራ እንድንሠራ መደረጉ በአጠቃላይ የመማሩ ሂደት የእርስ በርስ የመተጋገዝ ልምድን ፈጥሮልናል።	53.97	39.7	4.76	1.58	(+)
2	ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በመሆን በጋራ እንድንማማር መደረጉ በትምህርት ሂደት ራሳችንን ችለን የመሥራት ልምድ እንድናዳብር ረድቶናል።	49.2	42.8	4.76	3.17	(+)
3	እኛ ተማሪዎች እየተወያየን በጋራ ከምንማማር ይልቅ የሁሉንም ነገር መልስም ሆነ ትምህርት የሚነግረንና የሚያስተምረን መምህሩ ብቻ ቢሆን ይመረጣል።	6.34	19.04	28.6	46	(+)
4	በግል መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን ወይም ሓረጋትን በተገቢ ሥርዓተ ነጥቦች አሟልቶ የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት፣ የጊዜና የድርጊት ቅደም ተከተል ጠብቆ አንቀጽም ይሁን ድርሰት መፃፍ ይጨንቀኝ ነበር።	61.9	34.9	1.58	1.58	(+)
5	አሁን በተማርነው መሠረት የሚዘጋጁትን መልመጃዎች ብለማመድ ትምህርቱ አዝናኝና አሰደሳች ከመሆኑም ባሻገር የቋንቋ ችሎታዬን ለማሻሻል ይጠቅመኛል።	49.2	42.8	4.76	3.17	(+)
6	በዚህ በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የጽሕፈት ክሂልን በቡድን መማር ከጀመርኩ ወዲህ ሓሳቤን በጽሁፍ መግለጽ ብዙም አያስጨንቀኝም።	41.3	46	7.9	4.76	(+)
7	በዚህ ዓይነቱ ዘዴ ቋንቋን መማር ወድጀዋለሁ።	52.4	44.4	1.58	1.58	(+)
8	አሁን በተማርኩበት ዘዴ ድርሰት ስጽፍ ቅር ያሰኝ ነገር ነበር።	38	26.98	14.6	20.6	(+)

ከሠንጠረዥ-ለ፡-በመጠይቅ አንድ፣ ሁለት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት እና ሰባት የጽሕፈት ክሂልን በግል ከመማር ይልቅ በቡድን እርስ በርስ እየተረዳዱ እና እየተወያዩ መማር በጽህፈት ጊዜ በተማሪዎች ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ ስነ ልቦናዊ፣ስነ ልሳናዊ እና ስነ አእምሯዊ ገጽታዎችን በማስወገድ ትምህርቱን አዝናኝ እና አስደሳች ከማድረጉም ባሻገር የቋንቋ ችሎታቸውን እንደሚያሳድግላቸው የተስማሙት ተማሪዎች ቁጥር አማካይ በመትዮሽ ሲሳላ 94.60% ሲሆን በዚህ ያልተስማሙት ተማሪዎች ቀጥር በአማካይ 5.40% ናቸው።ከዚህ መረጃ መረዳት ሚቻለው ተማሪዎች የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራብ ቢማሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ ነው።

መጠይቅ ሦስትን በተመለከተም "እኛ ተማሪዎች እየተወያየን በጋራ ከምንማማር ይልቅ የሁሉንም ነገር መልስም ሆነ ትምህርት የሚነግረንና የሚያስተምረን መምህሩ ብቻ ቢሆን ይመረጣል" ለሚለው መጠይቅ የስምምነት ምላሽ የሰጡት 25.38% ሲሆኑ ያለመስማማት ምላሽ የሰጡት ግን 74.6% ናቸው።በዚህ መጠይቅ መረጃው የሚያመላክተው ሁሉም የትምህርት ክንውኖች በመምህሩ መተግባራቸውን አብዛኛው ተማሪ ያለመደፉን ነው።

በመጠይቅ ስምንት "አሁን በተማርኩበት ዘዴ ድርሰት ስጽፍ ቅር ያለኝ ነገር ነበር" በሚለው ሓሳብ የተስማሙት 64.98% ሲሆኑ 34.9% ያለመስማማት ምላሻቸውን የሰጡ ናቸው።ተማሪዎች በዘዴው መማራቸውን የሚፈልጉ ቢሆንም አንዳንድ ክፍተቶች መኖራቸውን የገለጹት አብዛኞቹ ተማሪዎች መሆናቸውን ያመላክተ መረጃ ነበር።

ሠንጠረዥ-3ሐ፡-ተማሪዎች በዘዴው ላይ ስላላቸው አመለካከት የሰጡት መረጃ

9.	የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዘዴ በቡድን መማርን የወደድኩበት ምክንያት፡-	የተማሪዎች ምላሽ (100 %)
ሀ	እርስ በርስ እየተዝናናንና እየተረዳዳን እንድንማማር የሚያደርግ በመሆኑ	39.2
ለ	የመማር ሂደቱ በአብዛኛው በእኛ በተማሪዎች ብቻ የሚከወን በመሆኑ	24.9
ሐ	በአብዛኛው ትምህርቱ የሚከወነው በመምህሩ በመሆኑ	1.6
መ	ተማሪው ትምህርቱን በጥሞና እንዲማርና እንዲከታተል ስለሚያደርግ በክፍል ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ርብሻና ጫጫታ የሚቀንስ በመሆኑ	3.2
ሠ	ይህ ዓይነቱ የመማር-ማስተማር ዘዴ ለእኛ አዲስ በመሆኑ	27.9
ረ	ሌላ	3.2

በመጠይቅ ዘጠኝ የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ ዘዴ በቡድን መማርን የወደዱበትን ምክንያት ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እየተዝናኑና እየተረዳዱ እንዲማማሩ የሚያደርግ እና የመማር ሂደቱ በአብዛኛው በተማሪዎች ብቻ የሚከወን መሆኑን የገለጹት ተማሪዎች ቁጥር በመትዮሽ ሲሰላ 64.1% ሲሆን በአብዛኛው ትምህርቱ የሚከወነው በመምህሩ መሆኑንና ይህ ዘዴ በክፍል ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ርብሻና ጫጫታ የሚቀንስ መሆኑን የገለጹት ተማሪዎች ቁጥር ደግሞ 4.8% ነው።ይህም በዚህ ዘዴ አብዛኛው ሥራ በመምህሩ መከናወኑን እና የክፍሉ ርብሻ የሚቀንሱ መሆኑን የተስማሙት ጥቂት መሆናቸውን እንዲሁም አብዛኛው ተማሪ ያለመስማማቱን ያመለክታል።በመቀጠል የመማር-ማስተማሩ ዘዴ አዲስ መሆኑን የገለጹት 27.9% ሲሆኑ ዘዴውን የወደዱበትን ምክንያት ሌላ በሚለው

መስፈርት ሥር ምርጫቸውን የገለጹት 3.2% ናቸው።በዚህም ዘዴው አዲስ መሆኑን የገለጹት ተማሪዎች መረዳት ይቻላል።

ሠንጠረዥ-3መ፡- በዘዴው ቅር ስለተሰኙበት ነገር ምክንያታቸውን የገለጹበት መረጃ

		ተማሪዎች ቁጥር
10	አሁን በተማርኩበት ዘዴ ድርሰት ስጽፍ ቅር ያለኝ ነገር፡-	
ሀ	የትምህርት ሂደቱ በአብዛኛው በመምህሩ የሚሸፈን በመሆኑ	0
ለ	የትምህርት ሂደቱ ተማሪውን የማያሳትፍ በመሆኑ	0
ሐ	ቀደም ሲል የማውቀው የመማር-ማስተማር ሂደት ሁሉም ነገር በመምህሩ የሚከወን በመሆኑ	14.3
መ	በክፍል ውስጥ በቡድን በሚደረገው ውይይት የክፍሉ ጸጥታ የሚደፈርስ በመሆኑ	74.6
ሠ	ሌላ	11.1

በአሥረኛው መጠይቅ ላይ "አሁን በተማርኩበት ዘዴ ድርሰት ስጽፍ ቅር ያለኝ ነገር" ለሚለው ሓሳባቸው በክፍል ውስጥ በቡድን በሚደረገው ውይይት የክፍሉ ጸጥታ የሚደፈርስ መሆኑን የገለጹት ተማሪዎች ቁጥር 74.6% በመሆኑ የዚህ ዘዴ ደካማ ጎኖች ከሚባሉት አንዱ የክፍሉን ጸጥታ መረበሽ መሆኑን መረዳት ይቻላል።ቀደም ሲል የመማር-ማስተማሩ ሂደት ሙሉ በሙሉ በመምህሩ የሚከወን በመሆኑ ጫናውን ሁሉ መምህሩ እንደሚያነሳላቸው የገለጹት ተማሪዎች ቁጥር 14.3% ነው።ከዚህ መረጃ በዚህ ዘዴ አብዛኛው ክንውን በመምህሩ መከናወኑን ብዙዎቹ ተማሪዎች ያለመስማማታቸውን መገንዘብ ተችሏል።እንዲሁም በዘዴው ላይ ቅሬታቸውን የገለጹት ተማሪዎች 11.1% መሆናቸውን መረዳት ተችለዋል።

ሠንጠረዥ-3ሠ፡-ተማሪዎች የቡድን ውይይቱን በመቶኛ ያሰሉበት መረጃ

11	በተለይ በክፍል ውስጥ በተማሪዎች በተደረገው የቡድን ውይይት የመማሩ ተግባር በመቶኛ ቢሰላ ምን ያህል ይሆናል ብለህ/ሽ ታስባለህ/ሽ?	የተማሪዎች ምላሽ (100%)
ሀ	100 %	44.4
ለ	90%	36.5
ሐ	80 %	12.7
መ	70%	4.8
ሠ	ሌላ	1.6

በመጠይቅ አሥራ አንድ ላይ "በክፍል ውስጥ በተማሪዎች በተደረገው የቡድን ውይይት የማስተማር ሂደት በመቶኛ ቢሰላ ምን ያህል ይሆናል" ለሚለው መጠይቅ መቶ በመቶ ያሉት 44.4%፣ዘጠና በመቶ 36.5%፣ሰማኒያ በመቶ 12.7%፣ሰባ በመቶ 4.8% ሲሆኑ ልላ ያሉት 1.6% ናቸው።ከዚህም የክፍል ውስጥ ክንውኑ በአብዛኛው በተማሪዎች መሸፈኑን ማረጋገጥ ይቻላል።

በአጠቃላይ ከጽሑፍ መጠይቁ የጽሕፈት ክሂልን በግል ከመማር ይልቅ በቡድን እርስ በርስ እየተረዳዱ እና እየተወያዩ መማር በጽህፈት ጊዜ በተማሪዎች ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ ስነ ልቦናዊ፣ስነ ልሳናዊ እና ስነ አእምሯዊ ገጽታዎችን በማስወገድ ትምህርቱን አዝናኝ እና አስደሳች ከማድረጉም ባሻገር የቋንቋ ችሎታቸውን እንደሚያሳድግላቸው እና ተማሪዎች የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ቢማሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ መረዳት ተችሏል።

ምዕራፍ አምስት

5 ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሓሳቦች

5.1 ማጠቃለያ

በመግቢያው እንደተጠቀሰው የጥናቱ ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በቡድን ማስተማር ለተማሪ ውጤታማነት ያለው አስተዋጽኦ ምን እንደሚመስል መከራዊ ጥናት በማካሄድ ማጣራት ሲሆን በሥሩ ለሚገኙ፡-

- በመምህር-ተኮር እና በተማሪ-ተኮር አቀራረቦች መካከል የታየው የተማሪ ውጤት ምን ይመስላል?
- በተማሪ-ተኮር አቀራረብ የሚገጥሙ ችግሮች ምን ምንድን ናቸው?
- ለገጠሙት ችግሮችስ መፍትሄ የሚሆኑት ሓሳቦች የትኞቹ ናቸው? ለሚሉ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል።

በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢ 9ኛ"G"ን መከራዊ ቡድን፣ 9ኛ"A"ን ጥበቅ ቡድን ብሎ ከመረጠ በኋላ መከራዊ ቡድን የሆነው 9ኛ "G" በተማሪ -ተኮር አቀራረብ በአጥኚው፣ ጥበቅ ቡድን የሆነው 9ኛ "A" ደግሞ በመምህር-ተኮር አቀራረብ በማስተማር የተሻለ ውጤት የሚያስመዘግበውን ቡድን ለመለየት መከራዊ ጥናት ተካሂዷል። ሁለቱ ቡድኖች በተለያየ የማስተማሪያ ዘዴ በተለያዩ መምህራን ከተማሩ በኋላ የሚያስመዘግቡትን ውጤት ለማወዳደር እንዲቻል ተማሪዎች የቅድመ ችሎታ ፈተና ተመዝነው ውጤታቸውም እንዲሁ በንጽጽር ቀርቧል።

በመሐራዊ እና በጥብቅ ቡድኑ መካከል ያለው የጽሕፈት ክሂል የቅድመ ችሎታ ምዘና አማካይ ውጤት ልዩነት 0.476 ነው።በመሆኑ በመካከላቸው ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት እጅግ ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል።

የዚህ አማካይ ውጤት የጉልህነት ደረጃ ከቲ-ቴስት ስሌት አንፃር ሲታይ የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ በማነሱ በሁለቱ ቡድን ተማሪዎች ውጤት መካከል ያለው ልዩነት የጎላ አይደለም።ይህ የሚያሳየው መሐራዊ እና ጥብቅ ቡድኑ በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ከመማራቸው በፊት የነበራቸው የጽሕፈት ክሂል ደረጃ ተቀራራቢ የነበረ መሆኑን ነው።

በመቀጠል ትምህርቱ ለሁለቱ ቡድኖች በተለያየ የማስተማሪያ ዘዴ በተለያዩ መምህራን ከተሰጠ በኋላ መሐራዊ ቡድኑ ከጥብቅ ቡድኑ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደቻለ የችሎታ ምዘና ውጤቶች ያመለክታሉ።

የመሐራ ትምህርቱ በተለያየ የማስተማሪያ ዘዴ ከመሰጠቱ በፊት ሁለቱ ቡድኖች በጽሕፈት ክሂል ችሎታ ተቀራራቢ ውጤት የነበራቸው ሲሆን፣ የመሐራ ትምህርቱ ለመሐራዊ ቡድኑ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ፣ ለጥብቅ ቡድኑ ደግሞ በመምህር-ተኮር አቀራረብ አማካይነት ከተሰጠ በኋላ ግን መሐራዊ ቡድኑ በአማካይ የ 9.2 ውጤት ብልጫ አሳይቷል።

የቲ-ቴስት ስሌት ውጤት እንደሚያሳየው ከጉልህነት ደረጃ አንፃር ሲታይ፣ የቲ-ቴስት ዋጋ ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ በመብለጡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት ታይቷል።በልዩነቱም የመሐራዊ ቡድኑ የጽሕፈት ክሂል ውጤት የተሻለ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል።

በአጠቃላይ በአማርኛ ቋንቋ የጽሕፈት ክሂልን በተማራ-ተኮር አቀራረብ ዘዴ በቡድን ማስተማር በተማሪዎች ላይ ሊፈጠር የሚችለውን ስነ ልቦናዊ፣ አእምሯዊና ስነ ልሳናዊ ጭንቀቶችን በማስወገድ፣የተማሪዎችን ተነሳሶትና ትጋት በከፍተኛ ደረጃ በመጨመር በተማሪዎቹ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ውጤታማነት ላይ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንደሚያሳድር ጥናቱ አረጋግጧል።

በመሠረታዊ ጥናቱ ወቅት በዋናነት ከጋጠመ ችግሮች መካከል፡- የተማሪዎች ዕውቀትና ፍላጎት አነስተኛ መሆን፣የክፍለ ጊዜ ሥርጭት ማነስ፣የክፍሉ ሁኔታ እና የተማሪው አቀማመጥ ለሥራው አመቺ ያለመሆን ችግሮች ጥቂቶቹ ናቸው።

86

5.2 የመፍትሔ ሓሳብ

የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው በአማርኛ ቋንቋ የጽሕፈት ክሂልን በተማሪ-ተኮር አቀራረብ በቡድን ማስተማር የተማሪዎችን ውጤታማነት ከማሳደግ አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።በጥናቱ ትምህርቱ በተለያየ የማስተማሪያ ዘዴ ከመሰጠቱ በፊት መሐራዊ እና ጥብቅ ቡድኑ በጽሕፈት ክሂል ችሎታ ተቀራራቢ ውጤት እንደነበራቸው በቅድመ-ምዘና ችሎታ ውጤቶች ተጣርቷል።

ትምህርቱ ለመሐራዊ ቡድኑ በተማሪ-ተኮር አቀራረብ፣ለጥብቅ ቡድኑ ደግሞ በመምህር-ተኮር አቀራረብ ዘዴ ከተሰጠ በኋላ ግን በሁለቱ ቡድኖች መካከል የውጤት ልዩነት ታይቷል። የችሎታ ምዘና ውጤቶች እንደሚያሳዩት መሐራዊ ቡድኑ በጽሑፍ ክሂል ምዘና በ9.2 አማካይ ውጤት ብልጫ አሳይቷል።

እንዲሁም ሁለቱ ቡድኖች በጽሕፈት ክሂል ያስመዘገቡት ውጤት የጉልህነት ደረጃ ከተ-ቴስት ስሌት አንጻር ሲታይ፣ መሐራዊ ቡድኑ ጉልህ የሆነ የውጤት ልዩነት አስመዝግቧል።

ይሁን እንጂ ይህንን ውጤታማ የሆነ የትምህርት የአቀራረብ ዘዴ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅፋት የሆኑት፡-

- ❖ የተማሪዎች ዕውቀትና ፍላጎት አነስተኛ መሆን፣
- ❖ የክፍለ ጊዜ ሥርጭት ማነስ፣
- ❖ የክፍሉ ሁኔታ እና የተማሪው አቀማመጥ ለሥራው አመቺ ያለመሆን

ችግሮች ጥቂቶቹ እንደሆኑ ተጠቅሷል።

የተማሪዎች እውቀትና ፍላጎት አነስተኛ መሆንን በተመለከተ፣መምህር-ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ለረጅም ጊዜ የቆዩበት ከመሆኑም ባሻገር በራሳቸው ጥረት

ከመማር ይልቅ ከጫፍ ጫፍ መምህራን እንዲያስረዱ የሚፈልጉ በመሆናቸው

ያላቸው እውቀት አነስተኛ፣አመለካከታቸውም የተዛባ ሊሆን ይችላል።ስለሆነም በቂ ማብራሪያ ተሰጥቶ የግንዛቤ ሥራ ተሰርቷል።

መከራዊ ቡድኑ በሳምንት ያላቸው ክፍለ ጊዜ ሁለት ሲሆን፣ ቀናቱም ዓርብና እሮብ፣ 3ኛ እና 4ኛ ክፍለ ጊዜያት ናቸው።በቀናቱ መካከል የአራት እና የአንድ ቀን ክፍተት አለ።በነዚህ ቀናት ተማሪዎች በቀዳሚው ክፍለ ጊዜ የተማሩትን የትምህርት ይዘት ሊረሱት ይችላሉ።አጥኚው ተማሪዎቹ ክፍለ ጊዜ በሌላቸው ቀናት የሚሰሩትን የቤት ስራ በመስጠት እና ተጨማሪ ትምህርት(ቱቶር) በመስጠት ችግሩን ለማቃለል የሞከረ ቢሆንም በሚመለከተው አካል የክፍለ ጊዜው ሥርጭት ከትምህርት ይዘቱ ጋር እንዲመጣጠን ቢደረግ ተመራጭነት ይኖረዋል።

የክፍሉን ሁኔታ እና የተማሪውን አቀማመጥ ለሥራው አመቺ ባይሆንም ሶስት ተማሪዎች በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ እንዲጠቀሙ እንዲሁም ፊትና ኋላ በመሆን በውይይት እንዲማማሩ በማድረግ ችግሩን ለጊዜው ለመቅረፍ ተሞክሯል።በቀጣይ ጊዜያት ግን የትምህርት ሥራ ከታለመለት ግብ እንዲደርስ የክፍል-ተማሪ ጥመርታው የትምህርት ሚኒስቴርን ደንብ ተከትሎ ተግባራዊ እንዲሆን የባለድርሻ አካላት ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ አጥኚው ይጠቁማል።

ቀቢ ጽሑፎች

ለማ ሰጠኝ (1998) "የተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ ዘዴ" በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ አስተባባሪነት ለትምህርት ባለሙያዎች ወርክ ሾፕ የተዘጋጀ።

(አዲሰ አበባ ያልታተመ)።

ሙሉጌታ ይታየው (2002) "የተማሪ ተኮር ትምህርት አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በሰርትፊኬት መርሀ ግብር እንደታየው።"አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት ቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለሁለተኛዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

መለሰ በዳኔ (1988) "የመማር ማስተማር ሂደት ለትምህርት ቤት አመራር ስልጠና የተዘጋጀ ማኑዋል።" አዲሰ አበባ (ያልታተመ)።

ማረው ዓለሙ (1987) "በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል የሁለተኛ ዓመት የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች በግልና በቡድን የሚጽፉ ድርሰቶች ንጽጽራዊ ጥናት።" አዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በመስተማር ዘዴ ለሁለተኛ ዲግሪ መሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

ማስረሻ አላዜ (2001) "በመርዓዊ ከተማ በአጸደ ህጻናትና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (1-4) የሚገኙ መምህራን የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው የጨዋታ ዓይነቶችና ክንውኖች" አዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በመስተማር ዘዴ ለሁለተኛ ዲግሪ መሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።

ሰይድ ይመር (1993) "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መጽሐፍ የቀረቡትን የጽሕፈት ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ለአማርኛ ማስተርስ ዲግሪ መሟያ የቀረበ።(ያልታተመ)።

ተስፋዬ ሽዋዬ (1981) "ሥነ ልሳንና ቋንቋን ማስተማር"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም (ያለታተመ)።

ትምህርት ሚኒስቴር (1994) "የትምህርት መስፋፋትና ጥራት ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው።" ለመምህራንና ርዕሰ መምህራን በተዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ የቀረበ(ያልታተመ)።

የሺጥላ መላትና ሌሎች (1996) "Active learning ምንነት፣የአቀራረብ ዘዴዎች፣ ጠቀሜታና አተገባበሩ።" በመምህራንና በልዩ ፍላጎት ትምህርት ማሰተባበሪያ ሥ/ት/ጥ/ም እንስቲቱት አዲስ አበባ።

ያለው እንዳወቅ (2001) የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር።አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ደረጀ ነጋሽ (1999) "የተማሪ ተኮር ተምህርት አቀራረብ አተገባበር ፍተሻ በደብረ ማርቆስ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ትምህርት ክፍል በ10+3 የስልጠና መርሃ ግብር።" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ(ያልታተመ)።

ደባሱ አስራት (1990) "የማስልጠኛ ዘዴዎች የስልጠና ማኑዋል" የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች ስልጠና መምሪያ።"አዲስ አበባ(ያልታተመ)።

Abraham Hagos, etal.(1999) "Teachers Teachers education hand book. Addis Ababa inistitute for curriculum Development and research ICDR.

Aggrawal,J.(1996) Principles, methods and Techniques of Teaching. Delhi:Vikas Publishing House.

